የብራና መጻሕፍት አሠራር እና አዘገጃጀት

ታምራት ሃይሉ[1]

Abstract

Parchment is a writing material which is made of prepared untammed animal skins such as goat, sheep and calf. This practice has been used as a writing medium for over two millennia. The term parchment is often used to refer to any animal skinthat has been scraped or dried under tension. Ethiopian Orthodox Tewahedo Church (EOTC) has given rise to rich artistic traditions, including vernacular literature, specifically Ethiopic manuscripts, also known as parchments, after the material on which they are written. Many of the materials needed to create the manuscript, such as parchment, ink, and pen, are fashioned locally, some by the artist himself by transforming goat skin into parchment, a laborious and meticulous process which includes stretching the skin on a wooden frame, removing the hair, washing and drying the skin in the sun or drying room, and repairing any holes. There are different types of manuscripts produced in Ethiopia. Some of them are mätsehaf, ketab or talsam and sənsul. The current study focuses only on the first type. The objective of this paper concentrates on showing and exploring how the birana metsihafoch or books are prepared, processed and worked in Estie wereda, south of Gondar in Amhara regional state. The study follows qualitative research design since it is mainly based on describing, analyzing and interpreting data. That is why; the researcher believs, descriptive method is better suited the study. The main data collection methods are participant observation and semi structural interviews.

Key words - folk, lore, folk belief, partchment, creativity.

[1] የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር የትምህርት ዘርፍ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በ፳፻ ዓ.ም. ተቀብለዋል፡፡ ተመራማሪው፣ በሙያቸው ጋዜጠኛ ሲሆኑ፣የቁም ነገር መጽሔት ባለቤትና ዋና አዘጋጅ ናቸው፡፡ በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ምክር ቤት ምክትል ሥራ አሥፈጻሚ ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡፡ ይህ ጽሑፍ በወቅቱ ካቀረቡት የመመረቂያ ጽሑፍ ተቀንጭቦ የወጣና ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥናት መጽሔት (JECS) በሚስማማ መልኩ ተስተካክሎ የቀረበ ነው፡፡ ሆኖም ግን ጽሑፉን ለማዳበርና ዘርዘር ያለ ዳራ ለመስጠት እንዲያስችል፣ በእግረ መንገድም ቢሆን ከ፳፻ ዓ.ም. ወዲህ በርእሰ ጉዳዩ ላይ የተደረጉ የጥናትና የምርምር ሥራዎችን ለማስተዋወቅ በማሰብ፣ በቅርቡ ለኅትመት የበቁ የጥናት ውጤቶችን በዋቢነት አካትቷል፡፡

፩. የጥናቱ ዳራ

ሳይንስና ቴክኖሎጂ እንደዛሬው ባልተስፋፋበት (በጥንት ጊዜ) ሰዎች ለኑሯቸው የሚያስፈልጉ ማናቸውንም ነገሮች ሠርተውና አምርተው የሚጠቀሙት በእጃቸው እንደነበር ይታወቃል። ሰዎች ለዕለት ተዕለት ኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን ከመሥራትና ከመጠቀም ባሻገር መንፈሳዊ ሕይወታቸውን ለማደስና ለማጽናትም ሲጠቀሙባቸው ኖረዋል። ከነዚህ መንፈሳዊ ሕይወትን በቀጥታ ከሚመለከቱ የእጅ ሥራ ጥበቦች መካከል ደግሞ የብራና መጽሐፍ ሥራ በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳል። የጥንት አባቶቻችን በኢትዮጵያ ብራና ፋቀው፣ቀለም በጥብጠው፣ብዕር ቀርፀው ያዘጋጇቸው የነበሩ የብራና መጻሕፍት የኅትመት ሥራ እስከተጀመረበት ጊዜ ድረስ በየአብያተ ክርስቲያናቱና በየገዳማቱ ውስጥ ሲዘጋጁ ቆይተዋል።

ኢትዮጵያ በዓለም ተለይታ ከምትታወቅባቸው ሀብቶች መካከል አንዱ የፊደልና የጽሑፍ ባለቤት መሆኗ ነው።

የሀገር ውስጥም ይሁኑ የውጭ ሀገራት ምሁራን፣ ኢትዮጵያ ጥንታዊ ሀገር ናት ሲሉ እንደማስረጃ የሚጠቅሱት የሀገሪቱን የብራና ጽሕፈት ታሪክና ትውፊት ነው። ነገር ግን እነዚህ ጥንታዊ የብራና መጻሕፍት በልዩ ልዩ መንገዶችና ስልቶች (ለምሳሌ ያህል በዝርፊያ፣ በስጦታ) ከሀገር እንዲወጡ ስለተደረገ የታሪካቸውን ያህል ለሀገር ሳይጠቅሙ ቀርተዋል (አምሳሉ፣ ፲፱፻፺፩፣ ገጽ ፴፱-፵)። በርግጥ ጽሑፍና ጽሕፈት ቀደም ብሎ በሐውልቶች፣ በመቃብሮች፣ በሳንቲሞች፣ በሕንጻዎች፣ በእንጨቶች ላይ ይተገበር እንደነበር በዘርፉ ጥናት ያደረጉ ተመራማሪዎች (ለምሳሌ ግርማ፣ ፲፱፻፺፬፣ ገጽ ፶፮) ያስረዳሉ። እነዚህ ጽሑፎች ዘመናቸውንና የዘመናቸውን መንፈስ ማለትም ፖለቲካዊና ታሪካዊ፣ ሃይማታዊና አፈ ታሪካዊ እንዲሁም ባህላዊና ትውፊታዊ ተግባሮችን፣ ድርጊቶችንና ሁነቶችን ቀርፀው ያስቀመጡና ለቀጣዩ ትውልድ ሰንደው ያኖሩ ናቸው። የእንስሳትና የአራዊት ቆዳዎች ተፍቀውና በልዩ ልዩ መሣሪያዎች ለስልሰው ንጹሕ ሠሌዳ ሲሆኑ፣ ብራናዎች ወይም የብራና ሠሌዳዎች በሚል ተሠይመው ለሥነ ጽሑፍ አገልግሎት ከመቅረባቸውና በጥቅም ከመገለጻቸው በፊት የቀደሙ ሰዎች እንደልብስ ይጠቀሙበት እንደነበር በቃል ተደጋግሞ ሲነገር እንሰማለን።

አምሳሉ (፲፱፻፺፩) በሀገራችን የብራና ጽሑፎች በጥቅም ላይ ከዋሉ ከ፲፻፭፻ ዓመታት በላይ ያስቆጠሩ እንደሆነ ቢገልጹም፣ የብራና ሥራ መቼና እንዴት ወደ ኢትዮጵያ እንደገባ ግን በትክክል አይታወቅም። ነገር ግን እስካሁን በተገኘው መረጃ መሠረት የብራና ሥራ ከመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ወደ ኢትዮጵያ እንደገባ ይገመታል።

ለዚህ ደግሞ ኢትዮጵያ ከነዚህ አገራት ጋር የነበራት የንግድና የባህል ግንኙነት እንደ ዋና ምክንያት ይጠቀሳል። Sergew (1981፣ p. 15) እንዲህ ይላሉ፤ "*ለስላሳ የጽሑፍ መሳሪያዎችን በኢትዮጵያ ጥቅም ላይ ማዋል የተጀመረው በትክክል ከመቼ ጀምሮ እንደሆነ እስካሁን አናውቅም። … ሀገሪቱ (ኢትዮጵያ) ከነዚህ ሀገራት ጋር የባህልና የንግድ ግንኙነት ስለነበራት ብራናው ከነዚህ ሀገራት መጣ ተብሎ ቢገመት ተገቢ ነው።*" Sergew እንደሚሉት ኢትዮጵያ የብራና መሥራች ከነበረችው ፔርጎሞስ ጋር የጠበቀ ወዳጅነት ነበራት። በተለይ ደግሞ በ፮ኛው ክፍለ ዘመን ወደ ኢትዮጵያ የገቡትን ዘጠኙን ቅዱሳን ለሙያው መተዋወቅ እንደ ምክንያት ይጠቅሳሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያ በቀንድ ከብት ምርት ከአፍሪካ ቀዳሚ አገር መሆኗን በመጥቀስ ለብራና መተዋወቅ የራሷን አዎንታዊ ሚና ተጫውታለች የሚሉ ወገኖችም አሉ። Assefa (1958, ገጽ 254) ይህንኑ ሀሳብ እንደሚከተለው ያጠናክራሉ፣ "በኢትዮጵያ የመጽሐፍ ሥራ ባህል ውስጥ ብራና የማዘጋጀት ጥበብና መጽሐፍን በእጅ የመጻፍ ሥራ ልዩ ቦታ የሚሰጠው ቅርስ ነው። በኢትዮጵያ ብራናን መሥራት ወይም ማዘጋጀት መቼ እንደተጀመረ በትክክል ለመናገር ያስቸግራል።

ያም ሆኖ የክርስትና ሃይማኖት ከተዋወቀበት ጊዜ ጋር ይያያዛል። ዘጠኙ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ በኋላ የመጀመሪያ ሥራቸው የነበረው መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ግእዝ ቋንቋ መተርጎም ነበር። ለዚህ ሥራ ይሆን ዘንድ የእንስሳትን ቆዳ መጠቀም ዓይነተኛ ዘዴ ሆነ። በአገራችን የብራና ላይ ጽሑፍ በአክሱም ዘመነ መንግሥት እንደተጀመረ የሚገመት ሲኾን ከዚያም በዛጉዌ ዘመነ መንግሥት እና በተለይም ደግሞ በመካከለኛው የታሪክ ዘመን የበለጠ ዳብሮ መገኘቱን ለመረዳት ተችሏል። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በአገራችን በጥንታዊነት ከሚታወቁት የብራና መጻሕፍት መካከል በአባ ገሪማ ገዳም /ትግራይ/ የሚገኘው አርባዕቱ ወንጌል ዋነኛው ነው። ይህ ብራና በድንቅ ሥዕሎች ያሸበረቀ እና የአባ ገሪማ ወንጌል በመባል የሚታወቅ ሲኾን ከ፭ኛው-፯ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደ ተጻፈ ይታመናል (መንግስቱ፣ ፳፻፱፣ ገጽ ፳፱-፴)። መንግሥቱ እንደሚሉት የብራና መጻሕፍት ዓለማዊ የብራና መጻሕፍት ዓለማዊ ጉዳዮችንም ሊያካትቱ ቢችሉም፣ በዋናነት ግን ለሃይማኖታዊ ጉዳዮች የሚውል ነው። ለዚህ ሊጠቀስ የሚችለው አንዱ ምክንያት የብራና መጻሕፍትን የሚያዘጋጁ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች መሆናቸው ነው። እነዚህ ባለሙያዎች ቀደም ባለው ጊዜ ያዘጋጁትን የብራና መጻሕፍት ወደ አክሱም ወስደው ወይም ልከው ከኤርትራ ለሚመጡ ሰዎች የመሸጥ ልማድ ነበራቸው። በሁለቱ አገሮች መካከል ያለው ድንበር ከተዘጋ በኋላ ግን ገበያው በመቋረጡ ሳቢያ የብራና መጻሕፍቱ ገበያ ቀዝቅዟል። ምንም እንኳን የአካባቢው የብራና መጻሕፍት ባለሙያዎች መጻሕፍቱን የሚያዘጋጁት ለዓለማዊ ሀብትና ጥቅም

ፍለጋ ባይሆንም፣ ሥራው ከሚፈልገው ረጅም ጊዜና የመሥሪያ ቁሳቁስ መወደድ የተነሳ ብዙዎቹ ሥራውን እየተዉት መጥተዋል፡፡ ራሳቸውንና ኑሯቸውን ለመደጎም ሲሉ ወደሌላ ሥራ መዞርን መርጠዋል፡፡ በዚህም የብራና አዘገጃጀት ሙያ ሕልውና አደጋ ላይ ወድቋል፡፡

ይህ ጥናት በደቡብ ጎንደር በእስቴ ወረዳ (ቦታውን የተጠቀሰው የጥናቱን መነሻ ለመጠቆም እንጂ የወረዳው የብራና ሥራ አዘገጃጀትና አሠራር ከሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች ይለያል ለማለት አይደለም፡፡ እንደዚያ ለማለት ንጽጽራዊ ጥናት ያስፈልጋልና ነው) ያሉ የብራና መጻሕፍት ደጓሽ ባለሙያዎች በሚያዘጋጇቸው የብራና መጻሕፍትና የአሠራር ሂደት ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የብራና መጻሕፍትን ለማዘጋጀት የሚውሉ ጥሬ እቃዎችና የአሠራር ቴክኒኮችን ከነመሳሪያዎቹ በመቅረፅ ላይ ያተኩራል፡፡ ይህን ጥናት ለማድረግ ያነሳሳኝ አንዱና ዋናው ምክንያት፣ ምንም እንኳን ሀገራችን ፊደልንና ጽሕፈትን ለዓለም በማስተዋወቅ ረገድ ቀዳሚ ከሚባሉ ሀገሮች ተርታ የምትመደብ ቢሆንም፣ በርእሰ ጉዳዩ ላይ በተለይም በተጠቀሰው አካባቢ ባለ የብራና መጻሕፍት ላይ የተደረገ ጥናት አለመኖሩ ነው፡፡[2] የዚህ ጽሑፍ አጠቃላይ ዓላማ የብራናን ምንነት ወይም የአሠራር ሂደት በኢትዮጵያ ዐውድ በተለይም በእስቴ ወረዳ (ደቡብ ጎንደር) ምን እንደሚመስል ማሳየት ነው፡፡ በዚህ አካባቢ የሚዘጋጁ የብራና መጻሕፍትን አዘገጃጀት በመመልከት ሂደቱንና የማዘጋጃ ቁሳቁሶችን ማጥናት ነው፡፡ ከዚህ አጠቃላይ ዓላማ በመነሳት ጥናቱ ሁለት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፤

፩. ለብራና መጻሕፍት ዝግጅት የሚያስፈልጉ ጥሬ ዕቃዎችን ዓይነትና ተግባር ከነሂደቱ ማሳየት፤

፪. የአዘጋጆቹን ሙያና ልምድ መግለጽ

የሚሉ ናቸው፡፡ ጥናቱ ዓይነታዊ የምርምር ንድፍን የተከተለ ሲሆን፣ ከዓይነታዊ የምርምር ዓይነት ደግሞ ገላጭ የምርምር ዘዴን ተከትሏል፡፡ ጥናቱ በዋናነት ከድርሳናት፣ ከቃለ መጠይቅና ከምልከታ የተገኙ መረጃዎችን በመግለጽ፣ በማብራራትና በመተንተን ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ በዚህም በቂ እውቀትና ልምድ ያላቸውን ዐሥራ አንድ መረጃ አቀባዮችን ቃለ መጠይቅ አድርጓል፡፡

[2] በብራና ላይ ጽሑፍን ማስፈር መቼ እንደተጀመረ ግልጽ ያለ መረጃ መኖሩን የሚያሳይ ማስረጃ አላገኘሁም። ነገር ግን ማስረጃ አለማግኘቴ (አለማግኘት) መረጃ የለም ወደሚል መደምደሚያ ሊወስደን የሚገባ አይመስለኝም።

፪. ብራናና የፎክሎር የጥናት መስክ

ከዚህ ቀጥሎ ባለው ንዑስ ክፍል ሥር ሁለት ጉዳዮች ያሉ ሲሆን፣ እነዚህም ስለብራና ምንነትና ታሪክ እንዲሁም ስለፎክሎር አጠር ያለ ማብራሪያ የሚሰጡ ናቸው።

፪.፩ ብራና ምንድን ነው?

ደስታ ተክለ ወልድ “ብራና” የሚለውን ቃል ሲፈቱ እንዲህ ይላሉ፤ “ብራና ማለት ከበግ፣ ከፍየል፣ ከጊደር፣ ከፈረስ ቆዳ ደደቡና ጸጉሩ ተፍቆ የተዘጋጀ፣ መጻፊያ፣ በነጭ ሆኖ ታጥቦ የጠራ የበራ ማለት ነው›” (፲፱፻፷፪፣ገጽ ፪፻፷)። ከሣቴ ብርሃን ተሰማ ደግሞ ‹‹የፍየል ወይም የበግ ቆዳ/ቁርበት/በመወጠሪያ እንጨት ተወጥሮ ሲደርቅ በሰላ መጥሪቢያ ከነጸጉሩ፣ ከነስግላጡ የሚሰገለጥ፣ የሚፋቅ፣ ተመልሶ ተራሞ ሲደርቅ በመዘገብ በልክ በልኩ እየተቆረጠ ለልዩ ልዩ መጻፊያ ኩኖ የሚጻፍበት ሠሌዳ›› (፲፱፻፶፩፣ገጽ ፫፻፵፩) እንደሆነ ይገልጻሉ። ‹‹የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትላንት፣ ዛሬና ነገ›› መጽሔትም በተመሳሳይ መንገድ ብራናን ‹‹የጥጃ ወይም የበግ ወይም የፍየል ቆዳ/አንጋሬ/በውኃ ተዘፍዝፎ በርጥቡ ተወጥሮ ተላጭቶ ጸድቶ የተቀረፀ ወረቀት መሰል የጽሕፈት ሠሌዳ ነው›› (፲፱፻፺፩፣ገጽ ፲፫) በሚል ይተረጉመዋል። ከእነዚህ ሦስት ምንጮች መረዳት የሚቻለው ብራና ለጽሑፍ መጻፊያነት የሚያገለግል ከከብት ቆዳ ወይም ቁርበት የሚዘጋጅ ሠሌዳ እንደሆነና ብራናውን ለማዘጋጀት የራሱ የሆነ ሂደት ያለው ባህላዊ ወይም በልማድ የሚከወን ሙያ ነው። ብራና፣ እንደ Harrison (1948, ገጽ 10) አቀራረብ፣‹‹parchment›› የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል የሚተካ ሲሆን፣ አሠራሩና አዘገጃጀቱ ባህላዊ መንገድን የተከተለ ነው። የፔርጋሞስ ንጉስ የነበረው Eumenes ከክርስቶስ ልደት በፊት በሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በታናሿ እስያ ለራሱ የግል ቤተ መጻሕፍት የማቋቋም ብርቱ ጉጉት ነበረው። የፔርጋሞስ ንጉስ Eumenes ከግብጽ ንጉሥ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ነበረው። ያኔ ግብጾቹ በፓፒረስ ምርት በዓለም የታወቁ ስለነበሩ የግብጽ ንጉሥ ከራሳቸው አልፎ ለሌሎች አገሮች ፓፒረስ /ወረቀቶችን/ ይሰጡ ነበር። የኋላ ኋላ ንጉሡ ካለው ዝናና ኃያልነት አንጻር ገናና ስሙና ክብሩ በጽሑፍ ይቀረፅ ዘንድ ባለመውደዱ የግብጽ ንጉስ ፓፒረስ ወደ የትኛውም ሀገር እንዳይሄድ ይከለክል ነበር። ይህ ሁኔታ አማራጭ የጽሕፈት ሠሌዳን ለመፈለግ ዕድል ከመፍጠሩም በተጨማሪ የእንስሳት ቆዳን በመፈቅፈቅ ለጽሑፍ መጠቀምን አስተዋውቋል።

Gaur (1979, ገጽ 26) ይህንን በተመለከተ ሲገልጹ፣ ‹‹የእንስሳት ቆዳን ለጽሑፍ መጻፊያነት የመጠቀም ጀማሪነት ከክርስቶስ ልደት በፉት ለነበረው ለእስያው የፔርጋሞስ ንጉስ የሚሰጥ ነው›› ይላሉ። Parchment የሚለው ሥያሜም Pargamum ከሚለው የንጉሡ

ሀገር ሥያሜ የተወሰደ ነው። በግሪክ pergameue ሲባል በላቲኑ ደግሞ pergamena እንዲሁም በፈረንሳይኛ parchemin ነው። የእንግሊዝኛ ደግሞ parchment ወደሚለው ሥያሜ አዘንብሏል። ሌላው የብራና ሥያሜ vellum የሚለው ቃል ነው። ቃሉ የparche-ment አቻ ወይም ምትክ ነው። ከሁለተኛው እስከ ስምንተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ገደማ ድረስ የብራና አሠራር በጥጃ (calf) ላይ የተመሰረተ ነበር። ጥጃ በፈረንሳይኛ velin የሚባል በመሆኑ ከዚሁ ተያይዞ vellum የሚለው ሥያሜ ተከሰተ። የብራና አመጣጥ ከሰው ልዩ ውስጣዊ ፍላጎት የመነጨ እንደሆነ አድርገው የሚገልጹ ምሁራንም አሉ። «ከጥንት ጀምሮ ሰዎች አስተሳሰባቸውንና ድርጊታቸውን ከትበው በማስቀመጥ ረገድ ተሳክቶላቸዋል። ቀርፀው ለማስቀመጥም ጠንካራ በሚባሉ እንደ ድንጋይ፣ እንጨት፣ ሸክላ፣ የዛፍ ቅርፊቶችና ቆዳዎች ባሉ ነገሮች ላይ ይጽፉ ነበር» (Harrison, 1948, ገጽ 2)። ሰዎች ያሳለፉትን የሕይወት ገጠመኝና የአኗኗር ሁኔታቸውን ለትውልድ እንዲተላለፍላቸው ይሻሉ። ለዚህ ደግሞ ለረጅም ጊዜ ሳይጎዳ የሚቆይ የጽሑፍ ክታብ /ማስቀመጫ/ መፍጠር ነበረባቸው። ከነዚህም መካከል ድንጋይ፣ እንጨት፣ ሸክላ፣ የተሰባበሩ የማሰሮ ገሎች፣ ቆዳዎች ይጠቀሳሉ። በድሮው ዘመን ህዝቦች መጻፍን ከተማሩ በኋላ የሚጽፉበትን ነገር አይመርጡም፤ መጻፍ በሚያስችል ነገር ላይ ሁሉ ይጽፉ ነበር። የኋላ ኋላ የሚጽፉበትን ነገር ማወቅ ከዚያም ማማረጥ ጀመሩ።

በብራና ሙያ በታሪክ ቀዳሚውን ቦታ የሚይዙት የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ናቸው። «ብራናን ለትውልድ እንዲተላለፍ ዘግቦ የማቆየቱ ዘዴ ጥንት የሥልጣኔ ምንጭ በሆኑት በምሥራቅ አገራት የተገኘ መሆኑን መገመት ይቻላል።» በማለት በሥልጣኔ ቀደምት የሆኑ ምሥራቃውያን ብራናን እንደጀመሩት ይታመናል (ዝኒ ከማሁ)። ለዚህ ደግሞ የግብጾች ፒራሚድ፣ ሙሴ በሲና ተራራ የተቀበላቸው የድንጋይ ላይ ትእዛዛት የዮርዳኖስ ወንዝን መሻገራቸውን ለመዘከር ሲል በ፲፪ኤል ነገዶች ልክ በ፲፪ ድንጋዮች ላይ ያስቀመጠው ጽሑፍ ለዚህ ማስረጃዎች ናቸው። የጽሕፈት ሥራና ከጽሕፈት ጋር የተያያዙ ሥራዎች የተጀመሩት በምሥራቅ አገሮች ዘንድ ነው ተብሏል። ከእነዚህ የምሥራቅ አገሮች ደግሞ ሜሶፖታሚያ ቅድሚያውን ትይዛለች። ከዚህች አገር ተነስቶ ነው የጽሕፈት ሥራ ወደ ሌላው ዓለም በተለይም የብራና ሙያ ትልቅ ደረጃ ደርሷል ወደሚባልለት የምዕራቡ ዓለም የደረሰው። በእርግጥ ሰሜን አፍሪካም ቢሆን የምሥራቁን ያህል የሚጠራበት ሁኔታ አለ። የብራና ሥራ ከላይ ከተጠቀሱት አገራት ቀጥሎ ፳ኤልና ፐርሺያ ደርሷል። ከዚህ በኋላ የሜዲትራንያንን ባሕር አቋርጦ ወደ ግሪክ፣ አሌክሳንድርያና ሮማ ገብቷል።

ፈቃደ ሥላሴ (፳፻፪) ብራና በኢትዮጵያ ስላለው መልክና ሁኔታ ሲናገሩ "ኢትዮጵያ ረጅም ታሪክ ያላት አገር` እንደሆነች ጠቅሰው፣ ሥነ ጽሑፍ በዓለም ላይ በውል

ባልታወቀበት ዘመን ኢትዮጵያ አገራችን በተለያዩ የሥነ ጽሑፍ መሣሪያዎች ፊደላትን ቀርፃ ለዛሬውና ለወደፊቱ ትውልድ መመኪያ የሚሆኑ የብራና መጻሕፍትን ማቆየቷ የማይካድ ነው::" እድሜ ጠገብ የሆኑት የብራና መጻሕፍት በተጻፉበት ጊዜ የነበረውን አስተሳሰብና ፍልስፍና አሁንም ድረስ ገጻቸው ሳይደበዝዝ ይዘው ይገኛሉ:: የብራና መጻሕፍት ዘመንና ትውልድ ተሻጋሪ ቢሆኑም ጥበቡም ሆነ ባለሙያዎቹ በአሁኑ ወቅት በሀገራችን ተገቢውን ትኩረት እያገኙ አይደለም:: ዘርፉን ማጥናት የአንድን ኅብረተሰብ የአኗኗር ሥርዐትና አስተሳሰብ ለማወቅ ይረዳል ተብሎ ይገመታል:: በሌላ በኩል ደግሞ፣ የብራና ሥራ በአገራችን ለብዙ ምእት ዓመታት የነበረ ቢሆንም የአሠራሩ ጥናትና ምርምር በክፍለ ዘመኑ ተመዝግቦ አልተቀመጠም ወይም አልተገኘም::[3]

፪.፪ ፎክሎር

"ፎክሎር" የሚለው ቃል ከሁለት ቃላት (`ፎክ` እና `ሎር`) የተገኘ ሲሆን፣ የመጀመሪያው ቃል ከሁለት በላይ ስብስብና ትስስር ያለውን የሰዎች ቡድን፣ ማኅበር፣ ተቋም፣ ማኅበረሰብ፣ ኅብረተሰብ ወይም/እና ሀገር የሚወክል ነው:: ሁለተኛው ቃል ደግሞ የዚህን ልዩ ቡድን፣ ማኅበር ወይም ተቋም፣ ማኅበረሰብ፣ ኅብረተሰብ ወይም ሀገር መገለጫና መታወቂያ የሆነውን ቁሳዊም ይሁን መንፈሳዊ፣ ባህላዊም ይሁን ዘመናዊ ዕሴት ወይም ሀብት ማለትም ባህልና ወጉን፣ የቤት አሠራሩንና የምግብ አዘገጃጀቱን፣ እምነትና ፍልስፍናውን፣ ዳንሱንና ሙዚቃውን፣ አልባሳቱንና የመዋቢያ መሣሪያዎቹን ወዘተ. የሚያመለክት ነው:: ስለሆነም ፎክሎር የሚባለው ሙያና ሙያው የያዘው ሐሳብ በሕዝብ አማካይነት ከአንድ ትውልድ ወደሌላ ትውልድ የሚተላለፈውን ማንኛውንም ዓይነት እምነት፣ ልማድ፣ ቁስ፣ ጥበብ፣ ታሪክ፣ አፈ-ታሪክ፣ ሚት ወዘተ. የሚያካትት ነው (Dundes, 1994)::

ከእነዚህ ዝርዝር የፎክሎር ወይም የባህል ዓይነቶች አንዱ እንደ ብራና ያሉ ተዳሳሽ ቁሶች የሚካተቱበት ቁሳዊ ባህል ነው:: ይኸኛው ዘርፍ ደግሞ፣ ፈቃደ (፲፱፻፺፩፣ ገጽ ፲፰) እንደሚያስረዱን፣ ከዘመናዊ ኢንዱስትሪ በፊት የነበረውን፣ የሰው ልጅ በእጁና በተፈጥሮ ባገኘው ልምዱና እውቀቱ የሠራቸውንና እየሠራቸው ያሉትን በዓይን የሚታዩትን፣ በእጅ የሚዳሰሱትን የመገልገያ ቁሳቁሶችን የሚይዝ ነው:: ቁሳዊ ባህል የፎክሎር አንድ ክፍል ነው:: ቁሳዊ ባህል በዓይን የሚታየውንና በእጅ የሚዳሰሰውን ሀገረሰባዊ ሀብት

[3] *በ የኢትየጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ 2000 ዓ.ም.* (፳፻፤ ገጽ ፪፻፫) በሚለው መጽሐፍ ውስጥ በክፍል ስምንት እንደቀረበው "በብራና የተጻፉ የግእዝ ቅዱሳት መጻሕፍት ብዙ መሆኑን ያሳያል። ከዚህ በተጨማሪም መጻሕፍቱ በሀገሪቱ በሚገኙ ልዩ ልዩ ገዳማትና ደሴቶች እንደሚገኙ፣ በሺህ የሚቆጠሩት ደግሞ በብዙ የአውሮፓ ብሔራዊ ዩኒቨርሲቲዎች አብያተ መጻሕፍት ውስጥ እንደሚገኙ ይጠቁማል።

ሁሉ ያጠቃልላል:: ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው ቁሳዊ ባህል ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ ቴክኒኮችን ሙያዎችን፣ የቁሶችን የአሠራር ሂደትና ዘዴዎችን የሚያቅፍ መሆኑን ነው:: በአንድ ባህላዊ ማኅበረሰብ ውስጥ ቤታቸውን እንዴት እንደሚሠሩ፣ ምግባቸውን እንዴት እንደሚያበስሉ፣ መሬታቸውን እንዴት እንደሚያርሱ፣ ዓሳ እንዴት እንደሚያሰግሩ የእርሻ መገልገያ መሣሪያዎቻቸውን እንዴት እንደሚያበጁ፣ የቤት ውስጥ ዕቃዎችን እንዴት እንደሚቀርጹ የሚያሳስብ ሙያ ነው:: እንዲሁም «ቁሳዊ ባህል በዓይን የሚታየውን፣ በእጅ የሚዳሰሰውን፣ ቁሶች የተሰሩበት ዘዴ ወይም ቴክኒክ የልዩ ልዩ ምግቦችን አሠራር የቅመማ ቅመም አዘገጃጀት ብልሃትን፣ የልብስ፣ የቤት፣ የአጥር ወዘተ አሠራርን የሰዎች ልዩ ልዩ ሥራዎችን የሚያከናውኑባቸውን መሣሪያዎችና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮችን ያጠናል» (ዝኒ ከማሁ) በማለት ቁሳዊ ባህል የሰው ልጅን ጠቅላላ የእጅ ሥራ ውጤት እንደሚያጠቃልል ያብራራል:: Dorson ስለቁሳዊ ባህል ምንነት ሲያብራሩ እንዲህ ይላሉ፤"

> … responds to techniques, skills recipes and formulas transmitted across the generation and … how men and women in tradition oriented societies build their home make their clothes prepare their food, farm and fish, process the earth's bounty fashion, their tools`` (1972፣ p. 3)::

ቁሳዊ ባህል ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ የቁሶችን የአሠራር ቴክኒኮችና ክፍሎች የሚያቅፍ ሲሆን አፈጣጠሩም በዘልማድ ነው:: እንደ ቁሳዊ ጥበብ ሁሉ በብዙ መልኮች የተሞላ ነው:: ወንዶችና ሴቶች በባህላቸው መሠረት ቤታቸውን እንዴት እንደሚሠሩ፣ ልብሳቸውንና ምግባቸውን እንዴት እንደሚያዘጋጁ፣ እርሻቸውን እንዴት እንደሚያርሱ፣ ዓሳ እንዴት እንደሚያጠምዱ፣ የእርሻ መሣሪያዎቻቸውንም በምን እንደሚሠሩና ተግባራዊ እንደሚያደርጉ እንዲሁም የቤት ዕቃዎቻቸውንና የማዕድ ቤት ቁሳቁሶችን እንዴት ዲዛይን እንደሚያደርጉ የቁሳዊ ባህል ተማሪው ሊያስብባቸው የሚገቡ ጥያቄዎች ናቸው:: ቁሳዊ ባህል የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችንና የእርሻ መሣሪያዎችን፣ የአደን ዕቃዎችን፣ ቅርጻ ቅርጽና ጌጣጌጦችን ባህላዊ ሥፍራዎችን ሁሉ የሚያጠቃልል ቢሆንም ዋና ዋና የሚባሉት ግን አራት ናቸው:: «በሀገረ ሰባዊ ቁሳዊ ባህል ሥር የሚጠቃለሉት ዘርፎች ሀገረ ሰባዊ እደ-ጥበባት ሀገረ ሰባዊ አልባሳት፣ ሀገረ ሰባዊ ኪነ ጥበባት እና ሀገረ ሰባዊ ሥነ-ሕንጻዎች ናቸው::» እንደ Dorson አገላለጽ ከቁሳዊ ባህል ገጽታዎች መካከል አንዱ ሀገረ ሰባዊ ዕደ ጥበብ ነው::

Glassie (1999፣ p. 41) እንደሚነግሩን ከሆነ፣ እነዚህን ቁሶች ለማጥናት ቢያንስ ሦስት ጉዳዮችን ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርብናል:: በመጀመሪያው ደረጃ፣ ቁሶቹ

የተሠሩበትን ንጥረ ነገር (አፈር፣ ብረት፣ እንጨት፣ ልብስ፣ ጥጥ፣ ቆዳ፣ ወዘተ.) መለየትና መረዳትን ይጠይቃል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ አሠራራቸውንና በሥራው ሂደት በቁሶቹ ላይ የፈሰሰውን ኪን ወይም ጥበብ፣ ዘዴ ወይም ቴክኒክ መመርመር ያስፈልጋል፡፡ ይህም የዚያን ፎክ ልዩ ኪሂልና የፈጠራ ችሎታ ለማየት ስለሚያስችል አእምሯዊ የእድገት ደረጃውን ለመረዳት ያስችላል፡፡ በሦስተኛ ደረጃ፣ ቁሱ ለምን ተሠራ? ውክልናው ምንድን ነው? ማንንስ ይወክላል? ትእምርታዊ ውክልናው እሱነቱንና ማንነቱን ይገልጻልን? የሚለውን መጠየቅና ተገቢ መልስ ማግኘት ያሻል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ፣ ባህላዊ ቁሶችን በምናጠናበት ወቅት፣ የቁሶቹን ቅርጽ፣ መጠን፣ ክብደት፣ ዓይነት፣ መቼት፣ ወዘተ. ማየትና ቁሶቹ ከፈጠራቸው ቡድን ወይም ማኅበረሰብ ጋር ያላቸውን ትእምርታዊ ዝምድናና ውክልና ማጤንንም ያካትታል፡፡ የዕደ ጥበባት ውጤቶች ቁስ ብቻ አይደሉም፡፡ ከቁስነታቸው በተጨማሪ በባሕሪያቸው በቅርጻቸው ወይም በይዘታቸው የሚያስተላልፉት አንዳች የሆነ መንፈሳዊ ዋጋ አላቸው፡፡ «እምነቶች በቁሳዊ ነገሮች አማካይነት ሊተላለፉ ይችላሉ፡፡ ቁሳዊ ነገሮች ሐሳቦች እና የፍርሃት ስሜቶች ወይም ሃይማኖታዊ ተመክሮዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡» በማለት የዕደ ጥበባት ውጤቶች ከሃይማኖታዊ እምነቶች ጋር የጠበቀ ዝምድና እንዳላቸው ገልጸዋል፡፡ የዕደ ጥበብ ውጤቶች ተብለው ጐልተው ከሚጠቀሱት መሣሪያዎች ውስጥ የእርሻና የአደን መሣሪያዎች፣ የሃይማኖት መገልገያ መሣሪያዎች /መስቀል፣ መቋሚያ ወዘተ/ የውበት ማጌጫ መሣሪያዎች /ቀለበት፣ አንባር፣ ጉትቻ ወዘተ/ ሸክላ ሥራ፣ ሽመና ሥራ፣ ብረታ ብረት ሥራ፣ ቆዳ ሥራ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ በሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ በብዛት የሚገኘውና /በገዳማት በጥንት ዘመን ሀይማኖታዊ መልእክቶችን ለማስተላለፍ ይጻፍ የነበረው የብራና ሥራ አንዱ ነው፡፡ ቀጥለን የብራናን ምንነት እንመለከታለን፡፡

፫. የብራና መጻሕፍት አሠራርና አዘገጃጀት

የብራና ሥራ ተጀመረ የሚባለው አንዳንዶች ከእርድ ነው ሲሉ ሌሎች ደግሞ ቆዳው ውኃ ሲዘፈዘፍ ነው ይላሉ፡፡ «እንስሳው ከመታረዱ በፊት መታጠብ አለበት፡፡ ሲታረድም ንጹሕ ሳር ላይ አስተኝቶ መሆን አለበት»፡፡ ከዚህ በኋላ ቆዳው ለብራና ማውጫ በተዘጋጀ ማፈፊያ ካራ መሳይ የብረት መሣሪያና በመረመሚያ ድንጋይ (pumuce stone) ይታሻል፡፡ ከዚያ በኋላ ቆዳው ፀሐይ ላይ ወይም እሳት ወይም ጭስ ባለበት አካባቢ ይሰቀልና እንዲደርቅ ይደረጋል፡፡ ቀጥሎ በመጥረቢያ (አነስ ባለ) በቆዳው ላይ የቀረው ጸጉር ይላጫል፡፡ Mellors and Parsons (2002) ቀጥሎ ያለውን ሃያት ሲገልጹ እንዲህ ይላሉ፡፡ «የቆዳው ዝግጅት ከተጠናቀቀና ቆዳው ሙሉ ለሙሉ ከደረቀ በኋላ ብራናው ቅርጹ ተቆርጦ የሚወጣበት ቦታ በጥንቃቄ መሳፈቻ በሚባል መሳሪያ

ከየማዕዘኑ ላይ ምልክት ይደረግበታል፡፡ ብራናውን ከማዕዘን እንጨቱ ላይ ተቆርጦ ከተላቀቀ በኋላ ሁለት ቦታ ላይ ይታጠፋል»፡፡ ቀጣዩ ሂደት ቅጠል ብራናው መሳፈቻ በሚባለው መሣሪያ በትንሹ ይበሳል፡፡ የብራናው ቅጠል (ከአንድ ቆዳ የሚወጣው) በቆዳው መጠንና በሚፈለገው የመጽሐፍ ዓይነት ይወሰናል፡፡ ከአንዱ ቆዳ ሁለት ሌላ ጊዜ ደግሞ አራት ወይም ስድስት ወይም ስምንት ነጠላ ብራናዎች ይወጣሉ፡፡

Sergew (1981፣ p. 17) ደግሞ ``ሂደቱ የሚጀምረው ከእርድ በኋላ ባለው ቆዳ መፋቅ ሳይሆን ቆዳው በውኃ ሲዘፈዘፍ ነው ይላሉ፡፡ በመጀመሪያ ቆዳው ውኃ ውስጥ ይነከራል፡፡ ቆዳው ውኃ ውስጥ የሚቆይበት ጊዜ እንደሁኔታው ይለያያል፡፡ ቆዳው /ትኩስ/ እንደታረደ ከሆነ ከሦስት ቀናት በላይ በውኃ ውስጥ መዘፍዘፍ አያስፈልግም፡፡ ነገር ግን ቆዳው ደረቅ ከሆነ /ቁርበት ሙሉ ሳምንት ምናልባትም ከዚያ በላይ የሆነ ጊዜ ሊፈልግ ይችላል፡፡ ከዚያም ቆዳው በአራት ማዕዘን እንጨት ላይ ይወጠራል፡፡ በሥጋው ገጽ ወደ ላይ ተደርጎ ንጹሕ ውኃ እየተጨመረ በመረመሚያ ድንጋይ በማሸት ስቡ እንዲለቅ ይደረጋል፡፡ ይህ ሂደት ስቡ እስኪወገድ ድረስ ለብዙ ጊዜ ይደጋገማል፡፡``ቆዳው ውኃ ውስጥ ከተዘፈዘፈ በኋላ የጊዜ ገደቡ (በውኃ ውስጥ የሚቆይበት) እንደ ቆዳው ዓይነት ሊለያዩ ይችላሉ፡፡ ቆዳው ትኩስ ከሆነ ጸጉሩና የሥጋው ክፍል በቶሎ የመልቀቅ ዕድሉ ሰፊ በመሆኑ በውኃ ውስጥ የመዘፍዘፍ ግዜው ያንሳል፡፡ ቀጣዩ ሥራ ቆዳውን ግድግዳ ላይ ወይም በተተከሉ እንጨቶች ላይ ሰቅሎ በመፋቂያ ድንጋይ ወይም ካራ ሥጋውንና ጸጉሩን ማስለቀቅ ነው፡፡ ከውኃው ያመለጠውና ከቆዳው ላይ ያለው አላስፈላጊ ንጥረ ነገር ከተወገደ በኋላ ቆዳው በውኃ ይታጠባል፡፡ ፀሐይ ላይ ይወጣል በሚፈለገው መጠን ለጽሕፈት አገልግሎትም ይውላል፡፡

የብራና አጻጻፍ የራሱ የሆነ የቆየ ስልት አለው፡፡ ሁሉም የቁም ጸሓፊዎች ማለት ይቻላል ብራና በሚጽፉበት ጊዜ ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ (የቀለም ቀንዶች) «የሚገለበጠው መጽሐፍ ከጸሓፊው በስተግራ የሚቀመጥ ሲሆን ሁለቱ የቀለም ቀንዶች አንዱ ጥቁር ሌላው የቀይ ቀለም ማስቀመጫዎች በስተቀኝ ይቀመጣሉ፡፡» የቀለም ጸሓፊው ዘወትር የሚጽፈው ወለል ላይ ተቀምጦ ነው፡፡ ይህ ካልሆነ ዝቅ ባለ ነገር ላይ ይቀመጣል፡፡ ብራናው ጉልበቱ ላይ (የግራ) አድርጎ ቀኝ እግሩን ዘርግቶ ነው የሚጽፈው፡፡ የቁም ጽሕፈት በብራና ላይ የሚጻፍበት የራሱ የሆነ ስልት አለው፡፡ ጽሑፍ የሚያርፍበት የብራና ክፍል ዓምድ ይባላል፡፡ አርእስት የሚባለው በመጽሐፍ በላይ በኩል የሚገኘው ባዶ ቦታ ሲሆን ኅዳግ የመጽሐፍ ግርጌ ከቀለሙ በታች እጅ የሚያርፍበት ቦታ ነው፡፡ ዐምድ የሚባለው ከብሌት እስከ ሐውልት፣ ከሐውልት እስከ ግሌት ያለው ቦታ ነው፡፡ ሐውልት ማለት ደግሞ ዐምዱን የሚከፍለው ቦታ ነው፡፡ ብሌት ከጥራዝ አጠገብ የሚገኝ የመጽሐፍ ማእከል ነው፡፡ ምስማክ/ብሌት የብራናው ዳርቻ ጠርዝ ነው (ከፍያለው፣

፲፱፻፹፮፣ ገጽ ፶፪):: ጥሩ ቁም ጸሓፊ እነዚህን ነገሮች በሚገባ ጠብቆ መጻፍ አለበት:: አለበለዚያ ካዛነፈው ይወቀስበታል የብራናው ጽሑፍ የተለያዩ ክፍሎችና ሥያሜዎች እንዳሉት ቀጥሎ የሰፈረው ሥዕል ያሳያል::

ሥዕል ፩፡ የብራና ጽሑፍ አንድ ቅጠል የጽሑፍ አቀማመጥ (ከፍያለው፣ ገጽ ፶፩)



፫.፩ የብራና መሥሪያ ጥሬ ዕቃዎችና አዘገጃጀታቸው

ለብራና ሥራ የተለያዩ ጥሬ ዕቃዎች ያስፈልጋሉ:: ከነዚህም መካከል ዋና ዋናዎቹ ቆዳ፣ ቀለምና ብዕር ናቸው:: በየሀገሪቱ ለብራና ሥራ የሚውለው የቆዳ ዓይነት አንድ አይደለም:: በአንዳንድ ቦታዎች የበግና የፍየል፣ በሌሎች ደግሞ የአሳማና የአህያ፣ በቀሪዎች ደግሞ የላም ወይም የጥጃ ቆዳ ይሆናል Harrison (1948) አብዛኛውን ጊዜ ለብራና የሚውሉትን ቆዳዎች ሲዘረዝሩ «የጥጃ፣ የበግ፣ የአሳማና ሌላው ቀርቶ አህያና የፍየል ይሆናል» በማለት ዘርዝረዋል:: የለሰለሰው ቆዳ ርጥብ ካልሆነ በውስጥ ለተወሰኑ ቀናት ከቆየ በኋላ ዳር ዳሩ ተበስቶ በፈረስ ጋማ ወይም ሞራ ይታሰርና በእንጨት ወይም በብረት ከመሬት ከፍ ተደርጎ ይወጠራል:: ከዚህ በኋላ በድንጋይ ወይም በብረት ላይ ይደረግና ውኃ የተጨመረበት በድንጋይ ይታሻል:: ከዚያ የሚገኘው የጠራ ቆዳ ነው ብራና የሚባለው:: አምሳሉ (፳፻፲፩፣ ገጽ ፳፬) በበኩላቸው `ብራና` የሚለው ቃል `ብርሃና` ከሚለው ስም የመጣ ሲሆን፣ ይህም የብራናው ቅጠል እንደ ብርሃን ነጭ

መሆኑን የሚያመለክት እንደሆነ ይገልጻሉ:: በዚህ ጥናት ውስጥ መረጃ የሰጡ ሁሉም ባለሙያዎች ደግሞ ብራና ማለት ከፍየል ቆዳ የሚዘጋጅ የጽሕፈት ወረቀት ወይም ሠሌዳ መሆኑን ይገልጻሉ::

«መጻፊያው ይዘጋጅ የነበረው ከእንስሳት ቆዳ ሲሆን በዋናነት የበግ ወይም የጥጃ ቆዳ ነበር፤ ከጥጃ ቆዳ ይዘጋጅ የነበረውና «ቬለም» በሚል ሥያሜ የሚታወቀው ቆዳ ተመራጭ ነበር::» በማለት ለመጻፊያነት የሚውለው የበግ ወይም የጥጃ ቆዳ ቢሆንም የጥጃ ቆዳ ይበልጥ እንደሚመረጥ ነው የገለጹት:: ሥርግው ከምን ከምን ሊዘጋጅ እንደሚችል እንዲህ ብለዋል:: ብራና ከቤትም ሆነ ከዱር እንሰሳት ቆዳ ይዘጋጃል:: ባለሙያዎቹ እንደሚሉት ብራና ከዶሮ ቆዳ እንኳን ማዘጋጀት ይቻላል:: ነገር ግን ያን ያህል በዶሮ ቆዳ የማዘጋጀት አስፈላጊነት የተለመደ አይደለም:: ብራና ላም፣ ጥጃ፣ ፈረስ፣ በግና ፍየል ለብራና ሥራ ዋናዎቹ የቤት እንስሳት ሲሆኑ ከዱር እንስሳት ደግሞ ሚዳቋና አጋዘን የሚዘወተሩ ናቸው:: ሀብተ ማርያም (፲፱፻፹፪፣ ገጽ ፪፻፹፱) ደግሞ «ለብራና መጽሐፍ ጥራት ያለው የፍየል ቆዳ ነው:: ነገር ግን የበግም ቆዳ ይሆናል» በማለት ከሌሎቹ በተሻለ ሁኔታ የበግና የፍየል ቆዳ ለብራና ተስማሚ እንደሆነ ጠቅሰዋል። Mellors & Parsons (2002) የሀብተ ማርያም ወርቅነህን ሐሳብ ይጋራሉ:: ምሁራኑ የፍየል ቆዳ ተፈላጊ የሆነበትን ምክንያት ሲያስረዱ:: «በብራና ላይ በአሁኑ ወቅት የሚጻፉ የቁም ጽሑፎች የሚዘጋጁት በአብዛኛውን ከፍየል ቆዳ ነው:: የበግ እና የላም ቆዳ በስፋት በገበያ ላይ የሚገኝ ቢሆንም የበግ ቆዳ ግን ጥሩ የጥራት ደረጃ የለውም:: የላምም ትልቅ ከመሆኑም በላይ ወፍራምና በዋጋ ደረጃም ውድ ነው» ይላሉ። ይህ ማለት ግን የፍየል ቆዳ በጠቅላላው ተመራጭ ነው ማለት አይደለም። ከፍየል ቆዳም የሚመረጥና የማይመረጥ አለ። ለምሳሌ ያህል የወንድም ይሁን የትንንሽ ሴት ፍየሎች ቆዳ ከትልልቅ ፍየሎች ቆዳ ይልቅ ተመራጭ ነው። ለዚህ ደግሞ እንደ ምክንያት የሚጠቀሰው የትንንሾቹ ፍየሎች ቆዳ ጥራት ያለውና በስብ (በዘይት) ያልተጠመቀ መሆኑ ነው::

ሁለተኛው ቀለም ነው:: የብራና መጻሕፍት የሚጻፉበት የቀለም ዓይነት በአብዛኛው ተመሳሳይ ነው:: ዋና ዋናዎቹም ሦስት ናቸው:: ሀብተ ማርያም «በቁም ጽሑፍ ለሚጻፉ መጻሕፍት በዋናነት የሚያገለግሉትና ለጽሑፍ ውበት የሚሰጡት የቀለም ዓይነቶች ቀይ፣ ሰማያዊና ወርቃማ ናቸው::» በማለት ገልጸዋል:: ቀይ ቀለም በግብጻውያን ዘንድ የመግቢያውን አንቀጽና የማስተዋወቂያ ቃላትን መጻፊያ ነው:: በግሪኮቹና በሮማውያን ዘንድ ደግሞ የቀይ ቀለም ግልጋሎት ከዚህም አለፍ ይላል:: «የጽሑፉን አንዳንድ ክፍሎች ለየት ለማድረግ የጽሑፉን የመክፈቻ መስመሮች፣ የንኡስ ክፍሎችን መነሻ ፊደላትና ርዕሱን በቀይ ቀለም ይጽፉ ነበር:: በቀይ ቀለም የተጻፉት ሩብሪክስ ይባላሉ::

ይህም ቀይ ከሚለው የላቲን ቃል የመጣ ነው።» ሌላው ጥሬ ዕቃ ብዕር ነው። ብዕር ወይም መቃ ከደረቅ የሸምበቆ ተክል የሚሠራ የቁም ጸሐፍያን መሣሪያ ነው። ብዕርን ከማንኛውም የተክል ዓይነት ማዘጋጀት የሚቻል ቢሆንም ግንዳቸው ክፍት በሆኑ የሳር ተክሎች የሚዘጋጀው የብዕር ዓይነት ዕድሜው ረዘም ያለ ነው። እንደ ሀብተ ማርያም አገላለጽ፣ ቀለም እንደ «የምጣድ፣ የድስትና የሌላም የማናቸውም ይህን የመሳሰሉ ከእሳት ከሚሰርሱት ዕቃዎች ጥላት ይዘጋጃል» (፲፱፻፹፪፣ ገጽ ፪፻፷፯)። ከዚህ በተጨማሪም ከክትክታ ቅጠል፣ ከቀርቅሃ ሸልፋፎች (ልባሽ) እና ከክሰል ብናኝ ሊሠራ ይቻላል። ከሰሉ ይፈጭና በንጹሕ እቃ ይታሻል። ዱቄቱ የሚታሸው የተለያዩ የእህል ዓይነቶች ተቆልተው ካረሩ በኋላ በውኃ ተቀቅለው በሚወጣው ንጥረ ነገር (አሲድ) ነው። ቀለሙ መያያዝና ስልባቦት ማውጣት ሲጀምር መድረሱ ይታወቃል። ከዚህ በኋላ ከግራር ወይም ከሌሎች እንጨቶች ሙጫ ሰብስቦ በመቀቀል በውኃው ቀለሙን ማሸት ያስፈልጋል። ይህም ለቀለሙ ወዝና ዕድሜ ይሰጠዋል።

ሀብተ ማርይም አያይዘውም ስለ ጥቁር ቀለም አወጣጥ ሲገልጹ ዋናው የጥቁር ቀለም መሥሪያ ንጥረ ነገር ካርቦን ነው በተለምዶ የሚዘጋጀው ከኩራዝ ጭስ ወይም ከድስት ጥላት የሚሰበሰብ ነው። ሌላው ዘመናዊ የጥላት ምንጭ ከባትሪ ድንጋይ የውስጥ ክፍል የሚገኝ ጥቁር ንጥረ ነገር እንደሆነም ጨምረው ያብራራሉ። ይህኛው አሠራር ከባትሪ ዝቃጭ (ከሰል ዱቄት) የሚሠራ ቀለም ነው። ቀይ ቀለም ለማዘጋጀት ሁለት ዓይነት መንገዶች አሉ የሚሉት Sergaw (1981) ስለአሠራሩ ሲያብራሩ እንዲህ ይላሉ። ዋናው ንጥረ ነገር መጀመሪያ ለማዘጋጀት ቀይ በርበሬ፣ የእንቁላል አስኳል ቀይ አፈርና ሙጫ ያስፈልጋል። እነዚህ አንድ ላይ በቆርቆሮ ጣሳ ከተቀላቀሉ በኋላ ለ፴ ቀናት ያህል ይበጠበጣሉ። የቀኑ ርዝመት ተፈላጊውን ጥሩ የቀይ ቀለም ውጤት ለማግኘት የሚያስችል ሲሆን ምናልባት ተጨማሪ ዐሥር ቀን መጨመር የበለጠ ጥሩ ውጤት ለማግኘት ያስችላል። ሁለተኛው ንጥረ ነገር የአበባና የተክሎች ሥር ነው። እነዚህን አንድ ላይ በመቀላቀል እንዲደርቅ ፀሐይ ላይ ይደረጋል። ከዚያም በእጅ ለሦስትና አራት ቀናት በአትክልት ውኃ ይቦካል። በመጨረሻም በቁራጭ ጨርቅ በማጥለል ደርቆ እንደኬክ እስኪጋገር መጠበቅ ነው። የቀለም አዘገጃጀት የራሱ የሆነ ሂደት ያለውና በጥንቃቄ በባለሙያው የሚዘጋጅ ነው። ባለሙያው አስፈላጊ የሆኑ ጥሬ ዕቃዎችን በማዋሃድ የሚዘጋጀው ቀለም ለብራና ጽሕፈት ሥራ ተመራጭ ነው።

ሦስተኛው ብዕር ነው። ብዕር ከሸንበቆ (መቃ) የሚዘጋጅ የመጻፊያ መሣሪያ ነው። ሸንበቆ ከሌሎች ዕፀዋት ተለይቶ ለዚህ አገልግሎት መዋሉ ጠንካራ ከመሆኑ የተነሳ ሙሉ ቀን እየነከሩ ቢጽፉበት ስለማይበሰብስ ነው። አንድ ወጥ ሆኖ የበቀለ ሸምበቆ ይቆረጥና ጢስ እንዲጠግብ ጢስ በሚወጣበት ቦታ ላይ ለብዙ ጊዜ ይቀመጣል። ከዚያ

ይወርድና በአንጓ በአንጓው እየተቆረጠ ይቀርባል። አቀራረጹ ሁለት ዓይነት ነው። የጉልህና የረቂቅ አቀራረጽ ይባላሉ። በጉልህ ብዕር የሚጻፉት መጻሕፍት አብዛኛውን ጊዜ የንባብ መጻሕፍት ሲሆኑ በረቂቅ ብዕር የሚጻፉት ደግሞ የዜማ መጻሕፍት ናቸው። "በአንጓ በአንጓ የተቆረጠበት ሽምበቆ በሰንጢ በጥንቃቄ ከተጠረበ በኋላ በጠባቡ መሃሉ ይሰነጠቃል። ቀለሙ በተፈለገው መጠን እየወረደ ለጽሕፈት ሥራው እንዲውል ይደረጋል።"

ሥዕል ፪፡ ረቂቅና ጉልህ ብዕሮች (ሐመረ ጽድቅ መጽሔት፣ ፲፱፻፺፪፣ ገጽ ፲፰ የተወሰደ)



Sergaw (1981) በበኩላቸው ስለ ብዕር እንዲህ ይላሉ። ብዕር ለማዘጋጀት ሽምበቆ ከመስክ ይቆረጥና ጭስ ሳያገኘው ደረቅ ቦታ ይቀመጣል። ጸሓፊው መድረቁን ሲያረጋግጥ ከ፲፮ ሴንቲ ሜትር ባልበለጠ ርዝመት ይቆርጠዋል። ከዚያም በአንዱ ጫፍ ይቀረጻል። ጫፉን ከመቁረጡ በፊት ጸሓፊው ምን ዓይነት ብዕር እንደሚያስፈልግ መወሰን አለበት። ጸሓፊው በትላልቅ ፊደላት ለመጻፍ የሚፈልግ ከሆነ ወፈር አድርጎ ይቆርጠዋል። አለበለዚያ ሹል ያደርገዋል። ከዚህ መረዳት እንሚቻለው ብዕር ከመሠራቱ በፊት የቁም ጸሓፊው በምን ዓይነት መንገድ መጻፍ እንዳለበት መወሰን አለበት። ጸሓፊው ተለቅ ባሉ ሆሄያት ለመጻፍ ካሰበ የሸንበቆውን ጫፍ ሰፊና ወፈር አድርጎ መቅረጽ በትንንሽ ፊደላት ለመጻፍ ካሰበ ደግሞ የሸንበቆው ጫፍ ቀጠን ማድረግ እንዳለበት ማወቅ ይገባዋል። ከዚህ በተጨማሪ ጥሩ ብዕር ለማዘጋጀት ሲፈለግ ሽምበቆውን ጭስ ያለበት ቦታ መስቀል ለብዕሩ ጥንካሬ ይሰጠዋል።

፫.፱ የብራና ማውጫ መሣሪያዎችና አገልግሎታቸው

የብራና አሠራር አድካሚና ውስብስብ ነው። ውስብስብነቱ ከሥራው ተደጋጋሚነት ብዛት የሚመጣ ነው። ነገር ግን ጠቅለል ባለ መልኩ ሲቀርብ ይህንን ይመስላል። «ቆዳው ውጫዊና ውስጣዊ ክፍሎች ከጸጉርና ከግልፋፊ ሥጋ ይጸዳሉ። ከዚያም ባለሙያዎች ወጥረው በፀሐይ እንዲደርቅ በማድረግ እንዲለሰልስ በመረመሚያ ድንጋይ ያሹታል»። Harrson (1948) ሂደቱ ይጀምራል የሚሉት ከእርዱ በኋላ ነው። የእንስሳው ቆዳ ከውጭ በኩል ጸጉር ከውስጥ በኩል ደግሞ ከቆዳው ላይ ተጣብቆ የቀረውን ሥጋ የብራናው ባለሙያ ይፍቅና ያጸዳዋል። ከዚያ በኋላ በመወጠሪያ እንጨት ወይም ብረት ይወጥረዋል። በመጨረሻም በሻካራ ድንጋይ ቆዳው ይለሰልስና ለጽሕፈት አገልግሎት ይውላል። እዚህ ላይ ሂደቱ የሚደጋገም መሆኑን ልብ ይሏል። ድንጋዩ በቆዳው ላይ የሚገኙትን ቆሻሻና የሥጋ ቅሪት እየገፈፈ ካነሳው በኋላ እንደገና ቆዳው በማፈፊያ (ካራ) ደህና ተደርጎ በባለሙያው እንዲላግ ይደረጋል። ቆዳው በደንብ ከደረቀ በኋላ ጸጉሩ በመጥረቢያ ይላጫል። መጥረቢያው ለመያዝ እንዲመች አጭር ተደርጎ የተሠራና ጫፉ ብራናውን እንዳይቀድ ዳርና ዳሩ ወደውስጥ በኩል የታጠፈ ነው። ብራናው ከደረቀ በኋላ ባለሙያው ቆርጦ ከመወጠሪያው ላይ ያላቅቀዋል ከዚያ በሚጻፈው መጽሐፍ መጠን እየተለካ ይሰመራል። መስመሩን ጠብቆ በወስፌ ውግ ይሰራለታል። “ውግ” ማለት ከአርእስቱ እስከ ኅዳጉ ያሉት መስመሮች ጠባብና ሠፊ እንዳይሆን በወስፌ በብራናው ዳር ላይ የሚደረጉ ምልክቶች እንደሆኑ ይገልጻሉ።

የብራና ማውጫ መሣሪያዎች ቁጥር መገደብ የሚቻል አይደለም። የመሣሪያዎቹ ቁጥር እንደ ጸሓፊው፣ እንደ ቦታው እና እንደ ብራናው ዓይነት ይለያያል። ሆኖም የጋራ የሚባሉ የብራና ማውጫ መሣሪያዎች መኖራቸው ብዙዎችን ያስማማል። የመጀመሪያው ማፈፊያ ነው፣ መሣሪያው ካራ የሚመስል የብረት ሞረድ ሲሆን ከቆዳው ላይ የተጣበቀን ሥጋ ማስለቀቂያ ነው። መላጫ ወይም መጥረቢያ ሁለተኛው መሣሪያ ሲሆን ከቆዳው ላይ ያለውን ጸጉር መላጪያ ነው። ሦስተኛው መወጠሪያ ነው። አራት ማዕዘን ቅርጽ ያለው እንጨት ሲሆን ብራናውን ወጥሮ የሚይዝ ነው። ሌላው መሰቀሪያ ሲሆን አገልግሎቱ በቆዳው ውስጥ እየገባ ለመወጠሪያ የሚሆን እንጨት ወይም ለበቅ (ዘንግ) የሚመስል ወይም ብረት እንዲገባ ቦታ የሚሰጥ ነው። አምስተኛው መራመሚያ ድንጋይ ነው። መራመሚያ ባለአንድ ድንጋይ ሲሆን ጸጉርንና ሥጋን በማስለቀቅ /ፈትጎ/ የብራናውን ጥራት የሚያረጋግጥ ነው። ከነዚህ በተጨማሪ ለመወጠሪያ የሚሆን ገመድ የብራናው መስመር የሚያወጣው ማስመሪያ /ወስፌ/

ብራናውን በቅርጽ በቅርጽ ለማውጣት የሚያገለግለው መቀስ /መቁረጫ/ እና ብራናው ቀለም እንዲቀበል የሚያደርገው መድመድ ተጠቃሽ መሳሪያዎች ናቸው፡፡

ሌላው ጉዳይ የብራና መጽሐፍ ሥራ ነው፡፡ ብራናው ላይ የሚጻፈው ሁሉ አስፈላጊ የውበት ቅቦች ከተከናወኑ በኋላ የመጨረሻ ሥራ የመጽሐፍ ስፌት ነው፡፡ Mollers and Parsons (2002) ስለመጽሐፍ ሥራ ሲናገሩ፣ የብራና መጽሐፍ ገጾች ይሰፉና አንድ ላይ ከእንጨት ገበታው ጋር ይያያዛሉ፡፡ ቀደም ባለው ጊዜ ለመስፊያ የሚያገለግለው ክር /ጅማት/ የሚገኘው ከከብቶች ጭን ነው፡፡ በዛሬው ጊዜ የፕላስቲክ ቁሶች ማለትም የፕላስቲክ ገመድ ወይም የመኪና ጎማ ውስጥ የሚገኝ ክር መጠቀም የተለመደ ነው፡፡ ቆየት ባለው ጊዜ የመጽሐፍ ሥራ በእንጨት ቦርዶች በቀጭኑ ተሸንሽኖ በከብት ቆዳ ይሰፋ ነበር፡፡ በአሁኑ ጊዜ ደግሞ በፕላስቲክ እና በጎማ ውጤቶችን ስፌቱ ይሰፋል፡፡ አሰፋፉ እንዲሁ የመጽሐፉ ክፍል የያዘውን ክር /ጎማ/ ጨርቅ ከሌላኛው ክፍል ክር / ጎማ ጋር አጠላልፎ መስፋት ነው፡፡

ሌላኛው የመረጃ ምንጭ[4] ደግሞ የአደንጎሱን ቅደም ተከተል ሲያስረዳ እንዲህ ይላል፡፡ መጀመሪያ ሽፋኑና ቆዳው በሙቀት ይለቀቅና አንድ ላይ በማጣበቅ በጨርቅ ይታሻል፡፡ በማግስቱ በማስመሪያ እየተለካ ልዩ ልዩ ቅርጽ ባላቸው መድጉሶች በእሳት እየጋለ እንዳይቃጠል በጥንቃቄ የተለያዩ ቅርጾች ይወጡለታል፡፡ በብዙዎቹ የብራና መጻሕፍት ላይ የሚወጡት ቅርጾች ሰባት ናቸው፡፡ እነዚህም መስቀል (cross)፣ ጭራ መድጉስ (horizontal lines)፣ ዓይነ ርግብ (dove's eye)፣ ቀርነ በግዕ (crescent)፣ ርዕሰ መድጉስ (criss cross)፣ ባለዘንባባ (paltn shape)፣ መርገጫ (stamp) እና የውኃ እናት (wave form) ናቸው፡፡ በትላልቅ መጻሕፍት ውስጥ ሁሉም ሰፍረው ሊገኙ ይችላሉ፡፡ በትናንሽ መጻሕፍት ላይ ግን ከእነዚህ ውስጥ ቢበዛ ሦስቱ ብቻ ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ እዚህ ላይ ቅርጾቹ ወይም ምልክቶቹ ለምን ሰባት ሆኑ የሚል ጥያቄ ሊቀርብ ይችላል፡፡ የብራና መጻሕፍትን የሚያዘጋጁ ባለሙያዎች ለዚህ ቀጥተኛ መልስ ባይሰጡም፣ ከልዩ ልዩ ክርስቲያናዊ ድርሰቶችና አስተምህሮት አንጻር ግን ጉዳዩ ከፍጹምነትና ከቅድስና ጋር ሊያያዝ እንደሚችል ተቀራራቢ መልስ መሰንዘር ይቻላል (Ginzberg፣1964፣ ገጽ 260)፡፡

[4] የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትላንት፣ ዛሬና ነገ መጽሔት (፲፱፻፺፬፣ ገጽ ፯)፡፡

ሥዕል ፫፡ ዝንዲው ቀይ ቀለም ሲቀባ

የብራና መጽሐፍ ሥራ ሦስት ደረጃዎች አሉት፡፡ የመጀመሪያው የመጽሐፍ ስፍ ይባላል፡፡ ከላይ እንደታየው ልዩ ልዩ የመጽሐፉን ክፍሎች እርስ በእርስ ማገናኘትና ማያያዝ ወይም መስፋት ማለት ነው፡፡ ቀጥሎ ያለው ሂደት ጥረዛ ሲሆን፣ ጽሑፎቹ የሠፈሩበትን የብራና ቅጠሎች (ወረቀቶች) ለአያያዝ በሚመች መልክ በጅማት ማያያዝ ማለት ነው፡፡ የጥራዝ ሥራ በሚከናወንበት ጊዜ በመጽሐፉ ዳርና ዳር ጠንካራ እንጨቶች /ገበታ/ ገብተው አብረው ይጠረዛሉ፡፡ የመጽሐፉ ገበታ አራት ቀዳዳዎች ይኖሩታል፡፡ የጥራዙ ጅማት በእነዚህ ቀዳዳዎች በመተላለፍ ይጠረዛል፡፡ ከዚያም የከብት ቆዳ / ባህረ ዐረብ/ ገበታው እንዲለብስ ተደርጎ በተለያዩ የመድጉስ መሣሪያዎች ይደጎሳል፡፡ ድጉሱ እንደተጠናቀቀ የቶታን ሥራ ይሠራለታል፡፡ «ቶታን ማለት መጽሐፉ ሲጠረዝ ከቆዳው ላይ በቀጭን ተሸንሽኖ የወጣውን ባሕረ ዓረብ (ዝንዲ) ትልታይ በትንሽ አፈ ምሳር መሳፈቻ እየተወጋ እንደ ሀረግ እርስ በእርስ እየተጠላለፈ ተጎንጉኖ በመጽሐፉ ራስጌ እና ግርጌ የሚገባ ጉንጉን ጌጥ ነው» (አበባው፣ ፲፱፻፺፱፣ ገጽ ፷፯)፡፡ በመጨረሻም የቶታኑ ጌጥ በመጽሐፍ ክፈፍ ዙሪያ ገብቶ ከተሰፋ በኋላ መጽሐፉ ኮረጆ በሚመስል ቤት ውስጥ ይገባል፡፡ ይህ ከከብቶች ቆዳ የሚሠራው የመጽሐፍ ቤት ማኅደር እየተባለ ይጠራል፡፡

፫.፫ ከብራና ሥራ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ሃይማኖታዊና ባህላዊ እሳቤዎች

እንደሚታወቀው የብራና መጽሐፍ ሥራ ከክርስትና ሃይማኖት ጋር ጥብቅ ቁርኝት አለው። ባለሙያዎቹም የፈለቁት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከሃይማኖቱ ተከታይ ቤተሰብ ነው። በብራና ላይ የተጻፉትና የሚጻፉት ጽሑፎች በአብዛኛው ሃይማኖታዊ የሆኑትም ከዚህ የተነሳ ነው። ስለሆነም ብራናውንና የአሠራሩን ሂደት አስመልክቶ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አማኞች ዘንድና ብራናውን በሚሠሩት ባለሙያዎች መካከል መንፈሳዊና ባህላዊ ስምምነት አለ። ስምምነቱ የቆዳውን ምንነት፣ የቀለሙን ዓይነት፣ የሥራ ቀናቱን፣ የጽሑፉን ይዘት የሚመለከቱ ናቸው። ብራናን አስመልክቶ የሚነሱትን እነዚህን ልማዳዊና ትውፊታዊ አመለካከቶችና እምነቶች ሀገረ ሰባዊ እምነቶች (folk beliefs) ይባላሉ።

የመጀመሪያው ሃይማኖታዊና ሀገረ ሰባዊ እምነት ከቆዳው ጋር ተያይዞ የሚቀርበው ነው። የብራና ሥራ ራሱን የቻለ አንድ ሙያ ቢሆንም ከሌሎች የፎክሎር ዘርፎች በተለይም ከሀገረ ሰባዊ እምነት ዘርፎች ጋር የጠበቀ ግንኙነት አለው። ሀብተ ማርያም (፲፱፻፹፪፣ገጽ ፪፻፹፱) ለብራና ሥራ ዋነኛ ግብዓት ስለሆነው ቆዳ አመራረጥ ሲናገሩ «ፈረስና አህያ እርኩሳን ናቸው የእነሱ ቆዳ በምንም ሁኔታ ለቅዱስ መጽሐፍ ሊውል አይችልም» ይላሉ። በብራና ሥራ ታሪክ ውስጥ አመለካከቱ ሥር የሰደደ ነው። ሌላው እምነት የሚገልጸው በቀለም መረጣ ነው። ለብራና መጽሐፍ ሥራ የሚሆነው የቆዳ ዓይነት የፍየል ቆዳ ነው። የፍየል ቆዳ ወፍራምና ነጭ በመሆኑ ለብራና መጽሐፍ ተስማሚ ነው፤ ቀለምም ይቀበላል። የበግ ቆዳ ከፍየል ቆዳ ጋር ሲነጻጸር በጣም ስስ ነው። ስስ ከመሆኑ የተነሳ በቀላሉ የሚላቀቅ ነው። የበግ ፀጉር ብዙ ስለሆነ ለመላጨት ያስቸግራል። በዚያ ላይ በቶሎ ይቀደዳል። ይሁን ተብሎ ቢዘጋጅ እንኳ ቀለም ሲያርፍበት በጀርባው በኩል ይወረዛል፣ ይጨማደዳል። የበሬና የላም ቆዳም ለብራና መጽሐፍ ሥራ አይመረጥም። የከብቶች ቆዳ ለብራና መጽሐፍ ሥራ አስቸጋሪ ነው። በተለይ የላምና የበሬ ቆዳ በጣም ወፍራምና ጠንካራ በመሆኑ ለብራና አይሆንም። የከብት ቆዳ የሚሆነው ለማጎደር ነው። ለብራና መጽሐፍ ሥራ ተመራጭ የፍየል ቆዳ እንደሆነ ቀደም ሲል ተመልክተናል። ከፍየሎች መካከልም የሴት ፍየል ወይስ የወንድ ፍየል ነው ለብራና ሥራ ተፈላጊው የሚል ተከታይ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ለብራና መጽሐፍ የሚመረጠው የሴት ፍየል ቆዳ ነው። ምክንያቱም የሴት ፍየል ቆዳ የመለጠጥና የመሳብ ባሕሪ አለው። ዘፍዝፈን አውጥተን ስንወጥረው ይሳባል። የተባዕቱ ቆዳ ግን አይሳብም።

ሥዕል ፬፡ ቆዳ በመረመሚያ ሲታሽ

የወንድና የሴት ፍየል ቆዳን በምን መለየት ይቻላል? የወንድ ፍየል ቆዳ ተገፎ የሚወጣው ከነብልቱ ፍሬ ነው። በመሆኑም ይህንን በመመልከት የሴት ፍየሎች ቆዳ ይመረጣል። ለብራና ሥራ ተመራጭ የሴት ፍየል ቆዳ ይሁን እንጂ የወንዱም ይህ ነው የሚባል መጥፎ ጎን የለውም። ነጋዴዎቹም ይህንን ጠንቅቀው ስለሚያውቁ የዋጋ ልዩነት አያደርጉባቸውም። የሞተ ፍየል ቆዳ ለብራና ሥራ አመቺ አለመሆኑን ባለሙያዎቹ ይናገራሉ። የሞተ ፍየል ሥጋው እንዳይበክት (እንዳይበላሽ) ለውሾች ተብሎ ቆዳው ተገፎ ቢወጣም ለቁርበት እንጂ ለብራና መጽሐፍ ሥራ አይጠቅምም። ሳይታረድ የሞተ ፍየል ወዲያውኑ ቢገፈፍ እንኳን ደሙ በቆዳው ላይ ስለሚሠራጭበት ጸጉሩ ተላጭቶ ለመጽሐፍ ሥራ ሲዘጋጅ ቀለም ያዥጎረጉራል። ሁለት ዓይነት መልክ ያመጣል። ደም የተሰራጨበት ቦታ ሲጠቁር ሌላ ቦታ ነጭ ይሆናል። በዚህ የተነሳ ሳይታረድ የሞተ ፍየል ቆዳ ለብራና ሥራ እንደማይፈለግ ባለሙያዎቹ ገልጸውልኛል።

ጥናቱ በተመሠረተበት በእስቴና አካባቢዋ (አጥኚው ጥናቱን የት እንዳካሄደ ለመጠቆም ያህል እንጂ የአካባቢው የብራና ሥራ ዓይነትና ሂደት ከሌሎች አካባቢዎች መለየቱን ለማሳየት አይደለም። እንዲያ ከሆነ ንጽጽራዊ ጥናት ማድረግ የግድ ይሆናልና) ለብራና መጽሐፍ የሚሆነው የቆዳ ዓይነት የፍየል ቆዳ ብቻ ነው። ሌሎቹ የቤት እንስሳት ቆዳዎች ለመጽሐፍ ሥራው አመቺ ባለመሆናቸው አይመረጡም። ከቤት እንስሳት ውጪ በጋማ ከብቶች ለምሳሌ በፈረስና በአህያ የሚዘጋጅ የብራና መጻሕፍት እንዳሉ ሲነገር የሚሰማ ቢሆንም ባለሙያዎቹ ፈጽሞ ሊሆን እንደማይችል ገልጸዋል። ቀኝ ጌታ[5] የኋላ የፈረስና የጋማ ከብቶች ቆዳ ለብራና መጻፊያነት ይውላል ወይ? በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ ‹‹ኸረገኝ ቀድሞውኑ እነሱን ማነው የሚያርዳቸው? የፈረስ ሥጋ የሰው ልጅ እንዳይመገብ በመጽሐፍ ቅዱስ ተከልክሏል፤ ሰኰናቸው ድፍን የሆኑ እንስሳት አናርድም፣ እንግዲያ ማነው ይህንን ርኩስ እንስሳ አርዶ ገፎ ቆዳው የሚያወጣው?›› በማለት የማይታሰብ እንደሆነና በሃይማኖትም እንዳልተፈቀደ ገልጸውልኛል ።

ብራና የእግዚአብሔር ቃል የሚያርፍበት በመሆኑ በርኩስ እንስሳት ቆዳ ላይ ቃሉን ማስፈር ያስቀስፋል ብለዋል። ሆኖም ግን መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ፍየልን የኀጥአን፤ በግ ደሞግ የጻድቃን ምሳሌ አድርጎ ነው የሚገልጻቸው። ታዲያ ብራና በፍየል ቆዳ መዘጋጀቱ እንዴት ይለያል? ቄስ ንብረቱ[6]፣

> *ፍየል በእርግጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የኀጥአን ምሳሌ ነች። ይህም የሆነው ሀፍረቷን ስለማትሸፍን፣ የዋለችበት ቦታ ስለማይታወቅ፣ እንደመጣች ስለምትቀባጥር ነው ጌታ ፍየልን የኀጥአን ምሳሌ ያደረገው በሕይወት ሳለች ነው እንጂ ከታረደች በኋላ መላ አካሏን አይደለም። በመሆኑም ሥጋዋ ታርዶ ይበላል። ቆዳዋም ቅዱስ ቃሉን ለማስፈር ተመርጧል*

በብራና መጻሕፍት ላይ ያሉት መስመሮች ብዛት ጎዶሎ ወይ ሙሉ መሆን ሀገረ ሰባዊ ትርጓሜ እንዳለው አንዳንድ ሰዎች ይገልጻሉ። የመስመሩ ብዛት ሙሉ ከሆነ አንዳች መቅሰፍት በጸሓፊው ላይ ሊመጣ ይችላል ተብሎ እንደሚታመን አሰፋ (፲፱፻፶፰፣ ገጽ ፪፻፷፫) ይገልጻሉ። ቄስ ንብረቱ ቦጋለ[7] ግን የመስመር ብዛቱን ማርቀቅ ወይም ማጉላት በጸሓፊውና በአጻፊው ስምምነት የሚወሰን እንጂ ከመቅሰፍት ጋር የሚያገናኘው ነገር እንደሌለ ይናገራሉ። ‹‹ብራናውን ስናሰምር የመስመር ብዛት ሙሉ ወይም ጎዶሎ ቁጥር

[5] ቃል መጠይቅ፣ሚያዚያ ፴፣፳፻

[6] ቃል መጠይቅ፣ሰኔ ፩ ፣፳፻

[7] ቃል መጠይቅ፣ሰኔ ፩ ፣፳፻

ይሁን ብለው አስበን የምናደረገው ነገር የለም። ሙሉ ስለሆነ አያስቀስፍም፣ ጎደሎም ስለሆነ አያጸድቅም። በብራናው ቅጽ ልክ ነው የምናስምረው። ከቅጹ ብንጨምርበት ጽሕፈቱ ይደቃል፣ ብንቀንስበት ደግሞ ይጎላል›› በማለት ሀሳቡን እንደማያምኑበት ገልጸውልኛል ።

ሌላው ሀገረ ሰባዊ እምነት ከቀለም ጋር የተያዘ ነው። ለብራና መጻሕፍት ሥራ ከሚያስፈልጉት ጥሬ ዕቃዎች መካከል ቀለም አንዱ ነው። በብዛት ጥቅም ላይ የሚውሉት የቀለም ዓይነቶች ደግሞ ጥቁርና ቀይ ቀለም ሲሆኑ አልፎ አልፎ ወርቃማ ቀለም አገልግሎት ላይ ይውላል። በንድፈ ሐሳብ ዳሠሣው ክፍል እንዳየነው ጥንታውያን ግብጾችም ሆኑ ግሪኮች ቀይ ቀለምን የሚጠቀሙት የመግቢያውን አንቀጽ ለመጻፊያ ነው። እኛ ሀገር ግን ከዚህ ለየት ያለ እምነት አለ። «ቀይ ቀለም በተለምዶ ጥቅም ላይ የሚውለው እግዚአብሔርን፣ የክርስቶስን፣ የማርያምን፣ የቅዱሳንንና የሰማዕታትን ስም ብቻ ለመጻፍ ነው። ቀለሙን ለማዘጋጀት ተፈጥሯዊ ንጥረ ነገሮች ማለትም ቀይ አበባና ቀይ አፈር ያስፈልጋሉ። ቀይ ቀለም የቅዱስነት መገለጫ ነው። የእግዚአብሔር ስሞች (አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ) የማርያም፣ የቅዱሳን፣ የመላእክት፣ የጻድቃን፣ የሐዋርያት፣ የነቢያትና የሰማዕታት ስሞች የሚጻፉት በቀይ ቀለም ነው። ሦስተኛው ሀገረ ሰባዊ እምነት በብራናው ላይ ያሉትን መስመሮች የሚመለከት ነው። በቁም ጸሓፊዎች ዘንድ ጎዶሎ እና ሙሉ መስመር (በቁጥር) ትርጉም አላቸው። መሪጌታ ገ/ሕይወት እንደሚሉት «በአንድ ገጽ የሚገኙ መስመሮች ጎዶሎ ቁጥር መሆን አለባቸው። የመስመሩ ቁጥር ሙሉ ከሆነ በጸሓፊው ላይ መጥፎ መቅሰፍት ሞትም ሊደርስበት እንደሚችል ይታመናል።» በዚህ ሐሳብ መሠረት ለምሳሌ በአንድ የብራና ገጽ ላይ ሃያ ስድስት መስመሮች ቢኖሩ በቁም ጸሓፊው ላይ ያልታወቀ መቅሰፍት ምናልባትም ሞት ሊደርስበት ይችላል ማለት ነው።

ሥዕል ፭ ጥቁር ቀለም ሲበጠበጥ

መሪጌታ ገ/ሕይወት[8]፤‹‹ቀይ ቀለም የፈጣሪንና የጻድቃን ስሞች ከመጻፍ በተጨማሪ መጽሐፍ አጽፊው አስጠርዝውና አስደጉሰው ለቤተክርስቲያን የሚሰጡ ነገሥታት ስሞችም አልፎ አልፎ በቀይ ቀለም ይጻፋል፡፡ ይህም የአክብሮት መግለጫ ነው›› ብለዋል:: የብራና መጻሕፍት በጥቁርና በቀይ ቀለም ከመጻፋቸው በተጨማሪ በወርቅማ ቀለምም የሚጻፉበት ሁኔታ አለ፡፡ ወርቅማ ቀለምን አልደረስኩበትም የሚሉት መሪጌታ ገ/ሕይወት በታሪክ ግን ስለ ወርቅማ ቀለም ተጽፎ አንብበናል ይላሉ ‹‹የእመቤታችንን ተአምሯን የጻፈው ደቅስዮስ በወርቅ ቀለም እንደጻፈ ይነገራል፡፡ ነገረ ማርያምን ደግሞ ዮሐንስ ወንጌላዊው እየነገረው በወርቅ ቀለም የጻፈው ተማሪው አብሮኮሮስ ነው ይባላል፡፡ እነዚህ ሰዎች ሀገራቸው የኢየሩሳሌም ሰማያዊት በመሆኗ ጌታ ተልጾላቸው በወርቅማ ቀለም ሊጽፉ ችለዋል፤ እኛ ግን ጥበብ ስላላደለን በቀይ ቀለም ነው አሁንም ድረስ የምንጽፈው›› (ዝኒ ከማሁ) በማለት ወርቅማ ቀለምን አዘጋጅቶ ለመጻፍ አለመቻል በተወሰነ ደረጃ ለእግዚአብሔር ክብር እንዳለመብቃት ተደርጎ እንደሚወሰድ ገልጸውልኛል፡፡

[8] ቃል መጠይቅ፣ ሚያዚያ ፳፤፳፻

ሦስተኛው ሀገረ ሰባዊ እምነት የሚመጣው ከብዕር ጋር ተያይዞ ነው። ከሸንበቆ ወይም ከቀርከሃ የሚዘጋጁት የብዕር ዓይነቶች ጉልህና ረቂቅ በመባል ይታወቃሉ። በጉልህ ብዕር የሚጻፉት መጻሕፍት በአብዛኛው የንባብ መጻሕፍት ናቸው። በረቂቅ ብዕር የሚጻፉት ደግሞ የዜማ መጻሕፍት ናቸው። በጉልህ ብዕር የሚጻፉ የብራና መጻሕፍትን የራሳቸው መለያና ምክንያት አላቸው። ጉልህ ብዕር የሚባለው በወፍራሙ ለመጻፍ የሚያገለግል የብዕር ዓይነት በመሆኑ ጎላ ጎላ ያሉ ፊደላት በመጠቀም የንባብ መጻሕፍቱ ይጻፋሉ። ለምሳሌ እንደ ስንክሳር፣ተአምረ ማርያም፣ድርሳነ ሚካኤል፣ገድለ ጊዮርጊስ የመሳሰሉት መጻሕፍት የሚጻፉት በጉልህ ብዕር ነው። ረቂቅ ብዕር ከገጻቸው ብዛት አንጻር አነስ አነስ ባሉ ፊደላት ለሚጻፉ የዜማ መጻሕፍት አገልግሎት ይውላል።[9] ለምሳሌ ጾሎተ ዕጣን፣ ሰኔ ጎሎጎታ፣ ድርሳነ ገብርኤል በረቂቅ ብዕር የሚጻፉ መጻሕፍት ናቸው። ከዚህ ሌላ ከሁለቱ የብዕር ዓይነቶች ትንሽ ረቀቅ የምትል "ረቂቅ ረቂቅ" የምትባል የብዕር ዓይነት አለች። ረቂቅ ረቂቅ ብዕር አገልግሎቷ የተገደፉ ፊደላት (ቀለማት) ባሉ ጊዜ ከራስጌያቸው ላይ በቀጭኑ የተገደፈው ፊደል እንዲገባ የምታደርግ የብዕር ዓይነት ነች። በጉልህ ብዕር የሚጻፉ መጻሕፍት መሀል ላይ በቀጭኑ የሚገቡ ዐረፍተ ነገሮች ወይም ሐረጋት ሲኖሩም በረቂቅ ረቂቅ ብዕር መጠቀም ይቻላል። ረቂቅ ረቂቅ ብዕር ከረቂቅ ብዕር የምትለየው ጫፏ በጣም ሹል መሆኑ ነው።

ሁሉም የብራና ጸሓፊዎች የተጻፈ ነገር የሚገለብጡ ናቸው። እግዚአብሔር ገልጾላቸው የሚደርሱ ሊቃውንት አልፈዋል። አሁን ስምንተኛው ሺህ ስለገባ የሚደርስ የለም፣ ቅኔ ብቻ ነው ዛሬ በየዕለቱ የሚደረሰው። ጸሓፊዎቹ የሚገለብጧቸው መጻሕፍት በአብዛኛው በግእዝ ቋንቋ የተጻፉ ቢሆኑም በአማርኛ የተጻፉ መጻሕፍትም እንዳሉ ተመልክቻለሁ። ለምሳሌ እንደ አክሲማሮስ፣ ሕማማተ መስቀል፣ ተአምረ ማርያምና መጽሐፍ ሄኖክ ዓይነት መጻሕፍት በአማርኛና በግእዝ የተጻፉ ናቸው። ጸሓፊዎቹ ለጽሑፍ የሚቀላቸው አማርኛው ሳይሆን ግዕዙ እንደሆነ ነው የሚናገሩት። ቀሲስ ኃይለ ኢየሱስ ‹‹በበኩሌ ለመጻፍ የሚቀለኝ ግዕዙ ነው። የተማርኩትም በደንብ የማውቀውም፤ ግዕዙ ውስጥ የሌሉ አንዳንዱ ቃላት ለምሳሌ እንደ ጨ፣ቸ፣ጀ፣ ዓይነት ቀለሞች ስላሉበትና ቅጥያም የሚበዛባቸው ፊደላት ስላሉ ይከብደኛል››

[9] *ጸሓፊዎቹ መሪጌታ ገ/ሕይወት፤ ቄስ ንብረቴና ቀሲስ ኃይለ ኢየሱስ የጽሕፈት ሥራቸውን ከመጀመራቸው በፊት ጸሎት ሲያደርጉ ተመልክቻለሁ። ዘወትር ሥራ ከመጀመራቸው በፊት አቡነ ዘበሰማያትና ውዳሴ ማርምን የሚደግሙ ሲሆን የዕለቱን ሥራቸውን ሲያጠናቅቁም ‹‹ስብሐት ለአብ፣ስብሐት ለወልድ፣ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ›› ብለው ነው። ከዚህ ሌላ አዲስ መጽሐፍ ለመጻፍ ሲዘጋጁ የመጀመሪው ቀን ‹‹ ጸሎተ ማርያም›› እመቤታችን በገባላት ቃል ኪዳን መሠረት ሥራችንን በሰላም አስጀምራ በሰላም እንድንጨርስ የምንማፀንበት ጸሎት ነው›› ብለውኛል (ቃል መጠይቅ ሰኔ ፱፣፳፱)።*

በብራና መጻሕፍት ውስጥ የእግዚአብሔር የእመቤታችን የሌሎች ጻድቃን ስሞች ለክብራቸው መግለጫ ሲባል በቀይ ቀለም እንደሚጻፉ ቀደም ሲል ጠቅሰናል። በተቃራኒው በመጻሕፍቱ ውስጥ የሰይጣን ስም ቢመጣስ ብዬ ጠይቄአቸው ቄስ ንብረቱ እንደሚከተለው ይመልሳሉ። “የሰይጣን ስም በመጽሐፉ ውስጥ ቢመጣ እንዳለ አይጻፍም፣ ፊደላቱ ቁልቁል ተገልብጠው ነው የሚጻፈው። ጻድቃን ሲከብሩ እሱ ሁሌ መዋረዱን ለማመልከት ሲባል ነው ተገልብጦ የሚጻፈው” ብለውኛል። ጸሓፊዎቹ የጽሕፈት ሥራቸውን ሲያከናውኑም ሆነ ፈጽመው አንድ መጽሐፍ ሲያጠናቅቁ ስማቸውን በመጽሐፉ ላይ ያሰፍራሉ። በመጽሐፉ መሀል ላይ ደግሞ የጸሓፊዎቹ ስም ብቻ ሳይሆን የአሳሳቢውና አጻፊ ሰው የክርስትና ስምም የሚጻፍበት ሁኔታ አለ። የሚገለበጠው መጽሐፍ ምን ጊዜም የሚቀመጠው በስተቀኝ ነው። መጽሐፍ ሲነበብ ሙሉ ለሙሉ አይገለጥም፣ በአንድ አቅጣጫ የሚነበብ ከሆነ በሌላ አቅጣጫ ያለውን ገጽ ጸሓፊው በጨርቅ ይሸፍነዋል። ለዚህ የሚሰጡት ምክንያት መጽሐፉ ክብር አለው፣ ሁሉም መጻሕፍት ቤተ መቅደስ ውስጥ ዕጣን እየታጠኑ የሚነበቡ ናቸው።

አራተኛው ሃይማኖታዊና ሀገረ ሰባዊ እምነት የሚፈጠረው ከሥራ ቀናት ጋር የሚተሳሰር ነው። የአካባቢው ኅብረተሰብ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታይ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ በወሩ ውስጥ በርካታ ሃይማኖታዊ በዓላት ይከበራሉ። ከዚህ ጋር በተያያዘ ዓመታዊ የንግሥ በዓል በሚውልበት ቀን የብራና ሥራ ፈጽሞ መሥራት እንደሌለበት ይሠየማል። ዋና ዋናዎቹ ቀናት የቅዱስ ሚካኤል ዕለት በ፲፪፣ የእመቤታችን ቀን በ፳፩ እና ጌታ የተወለደበት ዕለት በዓለ ወልድ በ፳፱ ብራና የማውጣት ሥራ አይሠራም። በእነዚህ ቀናት የብራና ማውጣት ሥራ ብቻ ሳይሆን እርሻ ማረስ፣ ማረም፣ መኮትኮት፣ ወፍጮ ማስፈጨት የተወገዘ በመሆኑ በእነዚህ ቀናት ሥራ አይሠራም። በርግጥ ይህ ሃይማኖታዊ ቀኖና እንጂ ሀገረ ሰባዊ እምነት ሊሆን አይችልም። የአከባቢው ኅብረተሰብ በአብዛኛው የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ በመሆኑ በእነዚህ ቀናት ሥራ ሲሠራ ያየው፣ ለቤተክርስቲያን አባቶች ተነግሮ ይወገዛል፣ እንዲገለል ይደርጋል። በመሆኑም ማንም ደፍሮ ወደ ሥራ የሚሰማራ የለም። በእስቴ ቀደም ሲል ከተገለጹት ወርኃዊ በዓላት ሌላ በሰንበት ሥራ አይሠራም። ከዚህ በተጨማሪ ግንቦት/ልደት፣ ለታኅሳስና ለሐምሌ ገብርኤል፣ ለዓመቱ ተክለ ሃይማኖት ሥራ አይሠራም። በዚህ ቀናት ሥራ ብንሠራ እግዚአብሔር ይቆጣል፣ ሥራችንን አይባርከውም ተብሎ ይታመናል[10]።

[10] ቃለ መጠይቅ፣ ሰኔ ፪፣ ፳፻

የመጨረሻው ጉዳይ የጽሑፉን ይዘት የሚመለከት ነው፡፡ ብራና መጻሕፍት በአብዛኛው የሃይማኖት መጻሕፍት ናቸው፡፡ ከሃይማኖትም ሙሉ ለሙሉ የክርስትና ሃይማኖትን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ከሃይማኖት መጻሕፍት ሌላ በብራና ላይ መጻፍ አለመከልከሉን ቄስ ኢያሱ የኋላ ‹‹እኔ እስከማውቀው ጊዜ ድረስ ከክርስትና ሃይማኖት መጻሕፍት ሌላ ጽሑፍ በብራና ላይ አትጻፉ የሚል ቃል ኪዳን የለም፡፡ ስለዚህ መጻፍ ይቻላል ብዬ ነው የማምነው›› በማለት ሌላ ጽሑፍ ሊጻፍበት እንደሚችል ይገልጻሉ፡፡ ቀኝ ጌታ የኋላ እንግዳም[11] በብራና ላይ ከሃይማኖት ጉዳይ ውጪ የሆነ ዓለማዊ ጽሑፍ እንዳይጻፍ የሚከለክል ቃል እንደሌለ ያምናሉ፡፡ በባለሙያዎቹ በብራና ላይ ከክርስትና ሃይማኖት ጉዳዮች ውጪ ሌሎ ጽሑፎች ቢጻፉበት የሚከለክል ነገር እንደሌለ ገልጸዋል፡፡

መሪጌታ ገ/ሕይወት በብራና መጻሕፍት ውስጥ ስለሚሳሉ ሥዕላትና ሐረጋትም የሚባልና የሚታመንም ነገር አለ፡፡ በብራና መጻሕፍት ውስጥ የሚሳሉት ሥዕላት ታሪኩን ወደፊት የሚያራምዱና ቅደም ተከተሉን የጠበቁ መሆን እንደሚኖርባቸው ሠዓሊያኑ ያምናሉ፡፡ ሠዓሊያኑ ከቁም ጸሓፊው ጋር በግንባር ሳይገናኙ ስለሚሣለው ሥዕል ምንነት ማወቅ ይችላሉ፡፡ ሠዓሊያኑ የሚሥሉት መንፈሳዊ ሥዕላት በመሆኑ ጥብቅ ሃይማኖታዊ እምነት አላቸው፡፡ የጥንት አባቶች ማቅ ለብሰው፣ አመድ ነስንሰው፣ ጾመው፣ ሰግደውና አልቅሰው ሥዕል ይስሉ ስነለበር በእግዚአብሔር ቸርነት የሚያውቁትን ታሪክ ብቻ ሳይሆን የማያውቁትንም ታሪክ ገልጾ አሳይቶ እንዲስሉ ያደርጋቸው ነበር በማለት የእምነታቸውን ስፋት ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ሠዓሊዎቹ ሥዕላቱን ብራና መጻሕፍት ላይ መሳል ከመጀመራቸው በፊት በየዕለቱ ጸሎት ያደርጋሉ፡፡ ጸሎቱ ‹‹መልካም ሥዕል›› የሚባል ሲሆን ታሪኩን ተረድተው የሚሥሉትን ሥዕል በሚገባ እንዲሥሉት የማነሳሳት መንፈሳዊ ኃይልን ያጎናጽፈናል ብለው ያምናሉ፡፡ የሥዕል ሥራ ከፈጠራ ሥራ ጋር ተያያዥ በመሆኑ አልፎ አልፎ ለሚያጋጥም የስሜት መደበት ጸሎቱ መፍትሔ እንደሆነ ሠዓሊ መሐሪ ይገልጻል፡፡ ‹‹የመሥራት ፍላጎቴ ሲቀንስ በጸሎት ነው ፍላጎቴን የምመልሰው፡፡ ሳልጸልይ ሥራ አልጀምርም፡፡ ሳልጸልይ ጀምሬ ቢሆን እንኳን የተወሰነ ደቂቃ ከሣልኩ በኋላ የምሠራው ይጠፋብኛል፡፡ ስፀልይ ይለቀኛል›› በማለት ሥዕላቱን እንዳይሥል የሚፈትነው መጥፎ መንፈስ በጸሎት እንደሚቋቋመው ገልጾልኛል፡፡

[11] ቃል መጠይቅ፣ ሚያዚያ ፳፰፣፳፻

፬. መደምደሚያና አስተያየት

፬.፩ መደምደሚያ

ይህ ጥናት የተደረገው በደቡብ ጎንደር እስቴ ወረዳ የብራና መጻሕፍት አዘገጃጀትና ቁሳቁስ ላይ ነው:: ጥናቱን በቁሳዊ ባህል ላይ እንዲሆን ያስቻለው የአጥኚው በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ያለውን የቁሳዊ ባህል ጥናት ክፍተት የመሙላት ፍላጎት ነው:: የጥናቱን ቦታ ደቡብ ጎንደር እስቴ ወረዳ ላይ ያደረገው ወረዳዋ አሁንም ድረስ በብራና መጻሕፍት ዝግጅት ሙያ ላይ በርካታ ባለሙያዎች አቅፋ ያያዘች በመሆኗ ነው:: በመሆኑም ጥናቱ በእስቴ ወረዳ ያሉ ባለሙያዎች የብራና መጻሕፍትን እንዴት እንደሚያዘጋጁና የማዘጋጀት ቁሳቁሳቸውን በመግለጽ ሙያው ህልውናው እንዳይጠፋ ከማኅበረሰብ ልማት ጋር የማስተሳሰርን አስፈላጊነት መነሻ አድርጎ ተካሂዷል:: ወደ መስክ ከተወጣ በኋላ በዚህ ጊዜ ምልከታና ቃለ መጠይቅን እንደ ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ተጠቅሟል:: በምልከታና ቃለ መጠይቅ ወቅት ፎቶ፣ ቪድዮ፣ ካሜራ፣ ቴፕ ሪኮርደርና ማስታወሻ ደብተር የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ ሆነው አገልግለዋል:: በመሆኑም በጥናቱ የተሰበሰቡ ቀዳማይና ካልአይ መረጃዎችን በማጠናከርና በመተንተን ወደ ግቡ ለመድረስ ጥረት ተደርጓል::

የብራና መጻሕፍት ዝግጅት እስካሁን ድረስ አለመጥፋቱ የማኅበረሰቡን እምነት አስተሳሰብና ለሙያው ያለውን ጥልቅ ግንዛቤ ያሳያል:: ‹‹የብራና ሥራ ጠፋ ማለት ሃይማኖታችን ጠፋች ማለት ነው ብለው አባቶቻችን ነግረውናል፣ ስለዚህ እኛ ጥቅም ባናገኝበትም እንሠራዋለን›› በሚል ሃይማኖታዊ ስሜት እየተሠራ ያለው ሙያ እንደ በፊቱ ራሱን ችሎ ኑሮን ለመምራትና መተዳደሪያ ሊሆን እንዳልቻለ ግን መረጃ አቀባዮች ገልጸዋል:: አጥኚው በመስክ ቆይታው ወቅት ባለሙያዎቹ የተለያዩ መጻሕፍት ሲዘጋጁ መመልከት የቻለ ሲሆን ከነዚህም መካከል ተአምረ ማርያም፣ ስንክሳር፣ ገድለ ተክለሃይማኖት፣ አርሴማ ቅድስት፣ አርባዕቱ ወንጌላት ሲዘጋጁና በተለያየ ደረጃ ላይ ሆነው በትንተናውም ለብራና መጻሕፍት የሚያስፈልጉ ዋና ዋና ጥሬ ዕቃዎች ቆዳ፣ ቀለምና ብዕር እንደሆኑና ለብራና መጽሐፍ የሚመረጠው የፍየል ቆዳ እንደሆነ አጥኚው ተረድቷል::

የብራና መጻሕፍት ሥራ በአብዛኛው የወንዶች ሙያ ሲሆን፣ ሴቶች ምናልባት በቀለም ማውጣት ላይ ሊሰማሩ ይችላሉ:: የተፈጥሮ ሀብት መመናመንና ቴክኖሎጂ አንዳንድ በቤት ውስጥ ይዘጋጅ የነበሩ ጥሬ ዕቃዎችንና ቁሳቁሶችን በዘመናዊ ቁሳቁሶች ለመተካት እንዳስገደዳቸው ባለሙያዎቹ ተናግረዋል:: የግእዝ ቋንቋ እውቀት ለቁም ጸሓፊ የግድ

ሲሆን፣ አብዛኞዎቹ ባለሙያዎች ሙያውን ከቤተሰብ ወርሰው ነው የሚሠሩት። መጻሕፍቱ ሁሉም ሃይማኖታዊ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ የሚታመንባቸው ሀገረ ሰባዊ እምነቶች ያሉ አሉ። ቃል ግጥምና ትረካ ግን ለማግኘት አልተቻለም። የብራና መጽሐፍ ሥራ ከክርስትና ሃይማኖት ጋር ጥብቅ ቁርኝት አለው። ባለሙያዎቹም የፈለቁት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከሃይማኖቱ ተከታይ ቤተሰብ ነው። በብራና ላይ የተጻፉትና የሚጻፉት ጽሑፎች በአብዛኛው ለማለት በሚያስደፍር መልኩ ሃይማኖታዊ የሆኑትም ከዚሁ የተነሳ ነው። ስለሆነም ብራናውንና የአሠራሩን ሂደት አስመልክቶ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስቲያን ማኅበረሰብእና ብራናውን በሚሠሩት ባለሙያዎች መካከል ሃይማኖታዊና ባህላዊ ትስስርና ስምምነት አለ። ስምምነቱ የቆዳውን ምንነት፣ የቀለሙን ዓይነት፣ የሥራ ቀናቱን፣ የጽሑፉን ይዘት የሚመለከቱ ናቸው። ብራናን አስመልክቶ የሚነሱትን እነዚህን ልማዳዊና ትውፊታዊ አመለካከቶችና እምነቶች ሀገረ ሰባዊ እምነቶች (folk beliefs) *እንላቸዋለን። በዚህም መሠረት ከብራና አሠራርና አዘገጃጀት ጋር ያለው ሀገረ ሰባዊ እምነት ብራናው ከሚሠራበት ቆዳ፣ ቀለም፣ ብዕር እንዲሁም ከሥራ ቀናት እና ከጽሑፉ ይዘት ጋር የተያያዘ ሆኖ ቀርቧል።*

፬.፪ አስተያየት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት እና መምህራን እንደ ብራና፣ ብዕር እና ቀለም የመሳሰሉትን የጽሑፍ መሣሪያዎች አዘጋጅተው ፊደላትን ቀርፀዋል። በዚህም ምክንያት ድንቅ በኾነው የእጅ ሥራቸው ለትውልድ የተሻገሩ አያሌ የብራና መጻሕፍትን አበርክተዋል። እነዚህ ሊቃውንት እና መምህራን በዚህ ድንቅ ተግባራቸው ሃይማኖታቸውን፣ ባህላቸውን፣ ታሪካቸውን እና ቅርሳቸውን ለትውልድ ከማውረሳቸውም ባሻገር አገራችን ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ተለይታ የምትታወቅበት የራሷ የኾነ ሥነ ፊደል እና ሥነ ጽሕፈት እንዲኖራት ያደረጉ ባለውለታዎች ናቸው። በትንተናው ክፍል ለማሳየት እንደተሞከረው፣ በእስቴ ወረዳ የሚገኘው የብራና አሠራር፣ የቀለምና የብዕር አዘገጃጀት፣ የሐረግና የሥዕል ንድፍ የራሱ ሀገራዊ መለያና ትውፊት ያለው ነው። ይህ ተግባር ቤተ ክርስቲያኗ ትምህርተ ሃይማኖቷ፣ ሥርዐቷ እና ትውፊቷ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ ከማድረጉ ባሻገር፣ ለሀገር የትምህርትና ሥልጣኔ መስፋፋት ያበረከተው አስተዋጽኦ ላቅ ያለ ነው። ለዚህም ነው እንዲህ ዓይነቱን ዘርፍ ማጥናት የቤተ ክርስቲያኗን ታሪክና ትውፊት ብቻ ሳይሆን የሀገሪቱን የትምህርትና የሥልጣኔ እንዲሁም የኅብረተሰቡን የአኗኗር ሥርዓትና አስተሳሰብ ለማወቅ ዓይነተኛ ሚና ይጫወታል ተብሎ የሚታመነው። ፈቃደ ሥላሴ (፲፱፻፪) "ሥነ ጽሑፍ በዓለም ላይ በውል ባልታወቀበት ዘመን ኢትዮጵያ አገራችን በተለያዩ የሥነ ጽሑፍ መሣሪያዎች

ፊደላትን ቀርጻ ለዛሬውና ለወደፊቱ ትውልድ መመኪያ የሚሆኑ የብራና መጻሕፍትን ማቆየቷ የማይካድ ነው" ያሉትም ለዚህ ነው::

በመሆኑም የብራና መጻሕፍት ዝግጅት ጥንታዊ ትውፊቱን ሳይለቅ በብዛትና በጥራት በማዘጋጀት ሙያው በወጣቱ ትውልድ ልቡና ውስጥ ሠርፆ የኑሮ መሠረት ሊሆን እንዲችል ለማድረግ ከዚህ በታች ያሉት አስተያየቶች ትኩረት አግኝተው ተግባር ላይ ቢውሉ ተገቢ ነው በማለት አጥኚው አቅርቦአል::

- የክልሉ መንግስት/የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት/ የብራና መጻሕፍት ዝግጅት በቋሚነት እየተሠራ ያለበትን ቦታ ትኩረት ሰጥቶ በማስተዋወቅ ቦታውን የብራና መጻሕፍት ዝግጅት ማእከል በማድረግ ለጎብኚዎች ሁኔታዎችን ቢመቻችና ሙያው ባህላዊ ገጽታውን ሳይለቅ መሥራት እንዲቻል የጊዜና የሀብት ብክነትን ሊያስወግድ በሚያስችል መልኩ በባለሙያዎች ጥናት ቢደረግና ሥልጠና ቢሰጥ፤
- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በአገሪቱ በልዩ ልዩ አካባቢዎች (ለምሳሌ ያህል በእስቴና በአካባቢው) ያለው የብራና መጻሕፍት ሙያ ዳብሮና በልጽጎ ባለሙያዎቹን፣ የአካባቢውን ማኅበረሰብ፣ ቤተ ክርስቲያኑዋንና አገሪቱን የበለጠ እንዲረዳና እንዲያስተዋውቅ ትኩረት ብትሰጠውና ጥበቡን በስፋት ማሠራት የምትችልበት ሁኔታ ቢፈጠር፤
- ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ከትውልድ ወደ ትውልድ መተላለፍ ያለባቸውን የሀገሪቱን ታሪካዊ የወረቀት መዛግብት በብራና በማጻፍ ቅርስን ሳይበላሽ የማቆየት ተግባሩን ቢወጣ ወይም የብራና መጻሕፍት ማእከላትን አቋቁሞ ለጉብኝት ክፍት ቢያደርግ፤
- በየዓመቱ በርካታ ተማሪዎችን የሚያስመርቁ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትም በተለይም የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲና ሌሎች የመንግሥት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ለተማሪዎቻቸው የሚሰጧቸውን የትምህርት ማስረጃዎች ማለትም ዲግሪዎችን፣ ዲፐሎማዎችንና ሠርፍኬቶችን በብራና ላይ አሰርተው ቢሰጡ፤
- ከዚህ በተጨማሪም፣ በጉዳዩ ዙሪያ ብዙ ልምድ ያላቸውና በተግባር የተፈተኑ ባለሙያዎች በየዩኒቨርሲቲዎች በመጋበዝ ተሞክሮአቸውን ለተማሪዎች እንዲያካፍሉ ቢደረግ ሙያውን በተወሰነ መልኩ ሊታደግ ይችላል የሚል እምነት አለኝ::

ዋቢ ጽሑፎች

ሀብተ ማርያም ወርቅነህ:: (፲፱፻፹፪):: *ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት*:: አዲስ አበባ፤ (ማተሚያ ቤት የሌለው)::

ሐመረ ጽድቅ:: (፲፱፻፺፪):: በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በማኅበረ ቅዱሳን ጽ/ቤት ስር የሚታተም ወርኃዊ መጽሔት፤ሜጋ ማተሚያ ድርጅት::

መንግሥቱ ጎበዜ:: (፳፻፪):: በዓለም ቅርስነት የተመዘገቡ የኢትዮጵያ የብራና መጻሕፍት እና መዛግብት:: *የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ጥናት መጽሔት*፣ 1. ገጽ 18-25::

ተክለ ፃዲቅ መኩሪያ::(፲፱፻፷፯):: *የኢትዮጵያ ታሪክ ዛጉዬ* 2ኛ መጽሐፍ:: ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ ማተሚያ ቤት::

ታምራት ሃይሉ:: (፳፻):: "የብራና መጻሕፍት አዘገጃጀት በደቡብ ጎንደር እስቴ ወረዳ" [ያልታተመ የኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፍ]:: የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ::

አምሳሉ ተፈራ:: (፳፻፲፩):: *ነቅዐ መጻሕፍት፡ ከ600 በላይ በግእዝ የተጻፉ የኢትዮጵያ መጻሕፍት ዝርዝር* ከማብራሪያ ጋር:: ጃጃው ማተሚያ ቤት::

አበባው ይግዛው:: (፲፱፻፺፱):: *የቁም ጽሕፈት ሙያ በኢትዮጵያ*:: ዳሸን ማተሚያ ቤት::

ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ 2000 ዓ.ም.:: (፳፻):: አዲስ አበባ::

ከሣቴ ብርሃን ተሰማ:: (፲፱፻፶፩):: *ያማርኛ መዝገበ ቃላት*:: አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት::

ከፍያለው መራሒ:: (፲፱፻፹፯):: *የቤተ ክርስቲያን አስተዋጽኦ ሥልጣኔ::* ት.መ.ማ.ማ.ድ::

ደስታ ተክለ ወልድ:: (፲፱፻፷፪):: *ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት*:: አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት::

ግርማ ባቱ:: (፳፻፲፬):: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፡ (ከጥንት- ፲ኛው ክፍለ ዘመን):: ቅጽ አንድ:: ማዮን መጻሕፍት መደብር::

ፈቃደ ሥላሴ:: (፳፻፪):: *ጥንታዊ የብራና መጻሕፍት አዘገጃጀት::* አዲስ አበባ፤አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ::

ፈቀደ አዘዘ:: (፲፱፻፺፩):: *የሥነ ቃል መምሪያ*:: ኢንተርናሽል ጀርመናዊ የጎልማሶች መረዳጃ ተቋም::

Assefa Liban. (፲፱፻፶፰). Preparation of parchment manuscripts. Ethnological Society Bulletin, 8: 5-20.

Dorson, R.M. (1972). Folklre and folklife: An introduction. The University of Chicago

Dundes, A. (2007). The meaning of folklore፡ The analytical essays of Alan Dundes. (Edited and Introduced by Simon J. Bronne). Utah State University Press.

Febure, L. (1958). The coming of the book: The impact of printing. Lowe & Brydone limited.

Gaur, A. (1979). Writing materials of the East. The British Library.

Ginzberg, L. (1964). The legends of the Jews. The Jews Publishers Society.

Glassie, H. (1999). Material culture. University of Chicago.

Goldstein, K. S. (1964). A guide for field workers in folklore. Folklore Association Inc.

Harrison, F. (1948). A book about books. Butler & Tanner Ltd.

Haven, Geo. (1967). Authors and their publie in ancient times. Putnam Cooper Square Publishers Inc.

Levarie, N. (1968). The art and history of books. James H. Heinman Inc.

Mollers, J. & Parsons, A. (2002). Proceedings of the Six International Conferences on the History of Ethiopian Art. Addis Ababa University.

McMutrie, D. C. (1943). The book: The story of printing and book making. Oxford University Press.

Oring, E. (1986). Folk groups and folklore genres: An introduction. Utah State University Press.

Pinner. H. (1949). The world of books in classical antiquity. Cooper Square Publishers Inc.

Sergew Hable Selassie. (1981). Book Making in Ethiopia. Addis Ababa: Addis Ababa University.